# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ | 82ኛ ዓመት ቁጥር 017 መስከረም 17 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ




ፎቶ - ሃዲስ አብርሃ

# ጠብን በእርቅ በደልን በይቅርታ እያረሙ መኖር እንደሚገባ ተጠቆመ

## - የ2015 ዓ.ም የመስቀል ደመራ በዓል በድምቀት ተከብሯል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የሰው ልጅ ጠብን በእርቅ፣ በደልን በይቅርታ፣ ድህነትን በልማት ክህደትን በሃይማኖት እያረሙ መኖር እንደሚገባ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ገለጹ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ የ2015 ዓ.ም የመስቀል ደመራ በዓል ላይ ትናንት ባስተላለፉት መልዕክት እንዳሉት፤ እግዚአብሔር ፍጥረታትን አሳምሮ ቢፈጥርም በሂደት መጋጨት በሰው ልጆች ብቻ ሳይሆን በፍጥረታት ዘንድ ሁሉ የሚስተዋል ሆኗል። በመሆኑም የሰው ልጅ ጠብን በእርቅ፣በደልን በይቅርታ፣ድህነትን በልማት ክህደትን በሃይማኖት እያረመ መኖር አለበት ብለዋል።



ፎቶ - ሃዲስ አብርሃ

የመስቀልን በዓል ስናከብር ከመስቀሉ መገኘት ባሻገር ማስታወስ ያለብን መስቀሉ ከእኛ ምን ይፈልጋል የሚለውን ነው ያሉት ፓትርያርኩ፤ የመስቀሉ ዓቢይ መልዕክት በሰው ልጆች መካከል ሰላም፣ ፍቅር፣ እኩልነትና ይቅርታ ሰፍኖ የሰው ልጆች ሁሉ በሰላም እንዲኖሩ መሆኑን በመገንዘብ አስተምህሮውን መተግበር እንደሚገባ አሳስበዋል።

መጋጨት በፍጥረታት ሁሉ የሚስተዋል ነው ያሉት ብፁዕነታቸው፤ አምላካችን አዳም በመበደሉ ምክንያት ከረገመው እርግማን አንዱ ምድር እሾህና አሜከላ ታበቅልብሃለች የሚል በመሆኑ በምድር ላይ ጠብና ክርክር፣ በሰው ልጆችም መከራ ሲደርስ በስፋት ይስተዋላል። የዚህ ችግር መፍትሔው ደግሞ ይቅርታና እርቅ ነው ብለዋል።

የሰው ልጅ ጠብን በእርቅ፣በደልን በይቅርታ፣ድህነትን በልማት ክህደትን በሃይማኖት እያረመ መኖር እንዳለበት አሳስበው፤ ሰው ከሰው ጋር ይቅርና እግዚአብሔርም ከሰው ጋር የነበረውን ጥልና መለያየት ያስወገደው በእርቅና በይቅርታ መሆኑ የሚያሳየውም ይቅርታ በእግዚአብሔር ዘንድ ያለውን ተቀባይነት የሚያሳይ መሆኑን አስገንዝበዋል።

የሰው ልጅ በሰላምና በፍቅር ከመኖር የተሻለ አማራጭ የለውም ያሉት ፓትርያርኩ፤ ይህም እውን የሚሆነው ከራስ ወዳድነት ተላቀን ለሌሎች ማሰብ ስንጀምር ነው። በመሆኑም ባለፉት ዘመናት የሆነውን ሁሉ በማቆም ሰከን ብለን እግዚአብሔርን ማዳመጥ አለብን ብለዋል።

ጠብን በእርቅ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






## ‹‹የመስቀል በዓል ያለፈውን ፈተና የምናስወግድበትና ለመጪው ጊዜ ተስፋ የምንሰንቅበት ነው››

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የመስቀል በዓል ያለፈውን ፈተና የምናስወግድበትና ለመጪው ጊዜ ተስፋ የምንሰንቅበት ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ተናገሩ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ የመስቀል በዓልን አስመልክተው ባስተላለፉት የእንኳን አደረሳችሁ መልእክት፤ ደመራው ሲለኮስ ጨለማው በብርሃን፤ ቁርና

‹‹የመስቀል በዓል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## ‹‹ከጥላቻ ፍቅርን፣ ከመገፋፋት ወንድማማችነትን ከመስቀሉ በመማር አብሮነትን ልናስቀጥል ይገባል‹‹

- ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አበቤ

ገጽ 4






ገጽ 3

## ‹‹ባህላዊና ሃይማኖታዊ እሴቶቻችን የአንድነታችን ማሳያዎች ናቸው››

- የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት

# በልጽገው ለማበልጸግ የሚሠሩ አዕምሮዎች

**ጌትነት ምህረቴ**

ለትምህርት ወደ ቻይና አገር ሄዶ ትምህርቱን ተከታትሎ አጠናቋል። ቻይና ሲማር ሁሌም አገሩን የሚጠቅም አዲስ ቴክኖሎጂ ቀስሞ ሀገሩ ላይ ለመተግበር ነው ሀሳቡ ። ዛሬ ይህን ሀሳቡን ወደ ተግባር የሚለውጥበት ጊዜ ደርሷል። የፈጠራ ሀሳቡ ከመላው ኢትዮጵያ ከቀረቡ ከ200 የዲጂታል ቴክኖሎጂ ፈጠራ ሀሳቦች ጋር ተወዳድሮ ካለፉት 15 የፈጠራ ሀሳቦች አንዱ ሆኗል።በዚህም 260ሺህ ብርና ሰርተፍኬት ተሸልሟል። ወጣት ሄኖክ ተፈራ።

በአዲስ አበባ ከተማ ተወልዶ ያደገው ወጣት ሄኖክ በአሁን ጊዜ የፈጠራ ሀሳቡን ወደ መሬት ለማውረድ እየሠራ ነው። ለዚህም ሁሉንም ዝግጅት አጠናቆ፣ ቀን ቆርጦ፣ገንዘብ መድቦና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተነጋግሮ ወደ ተግባር ለመሸጋገር እየተንደረደረ መሆኑን ነግሯናል። 16 ሚሊዮን ሕዝብ የሚጠቀምበትን የአውቶብስ ትራንስፖርትና ሌሎች አገልግሎት ሰጭ ተቋማት ክፍያቸውን በካርድ የሚያደርጉበትን የፈጠራ ሀሳብ ወደ ሥራ ለማስገባትም ማሽኑን ለማሳያነት በሀገር ውስጥ መሥራት ችሏል።ማሽኑም ተሞክሮም ውጤታማነቱ ተረጋግጧል፤ ሶፍት ዌሩም ተዘጋጅቷል ሲል ገልጾልናል።

የፈጠራ ሀሳቡም አውቶብሶችን፣ ሸገር ዳቦ ፣ ፈጣን መንገዶችና መሰል ብዙ ሕዝብ የሚጠቀምባቸው ተቋማት ማስተር ካርድን በመጠቀም ክፍያ የሚፈጽሙበት ሥርዓትን መዘርጋት መሆኑን ይገልጻል። የፈጠራ ቴክኖሎጂውም ጊዜን ይቆጥባል፣የትኬት ወጪን ያስቀራል፣ የጥሬ ገንዘብ ግብይትን ያስቀራል ። ቴክኖሎጂውን በ2015 ዓ.ም በተመረጡ ቦታዎች ወደ ሥራ ለማስገባት እንደሚሠራም አስታውቋል።



በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር አዘጋጅነት በብሩህ ዲጂታል ቴክኖሎጂ የንግድ ፈጠራ ሃሳብ ውድድር ያሸነፉ 15 ተወዳዳሪዎች እያንዳንዳቸው የ260 ሺህ ብር ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። በውድድሩ አመርቂ የአይሲቲ የፈጠራ ሀሳብ ይዘው የቀረቡ 200 ሲሆኑ ከእነዚህ 20 ወጣቶች የፈጠራ ሥራ ተወዳድሮ 15ቱ አሸናፊ ሆነዋል። ከእነዚህ መካከል አንዱ ቃልአብ ሙሉጌታ ነው።የፈጠራ ሀሳቡ አርሶ አደሩን የእርሻ ሥራ ምርታማ እንዲሆን የሚያስችል ምክረ ሀሳቦችን የሚሰጥ ሶፍትዌር መረጃ ያበለጸገ ሲሆን ይህ ሶፍትዌር በተንቀሳቃሽ ስልኩ የተጫነለት እያንዳንዱ አርሶ አደር የግብርና ወቅታዊና ጠቃሚ መረጃዎችን በቀላሉ ማግኘት የሚያስችል መሆኑን ነግሯናል።

ይህም የፈጠራ ሀሳብ ለአርሶ አደሩ በግብርና ሥራው ውጤታማ መሆን የሚያስችለው መሆኑን አመልክቶ፤ መንግሥት ያቀደውም ምርትና ምርታማነት በእጥፍ የማሳደግ ግብ ለማሳከት የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ይኖረዋል የሚል እምነት አለው።ይህን ተግባራዊ ለማድረግም ከግብርና ሚኒስቴር ጋር በትብብር ለመሥራት ምክክር መጀመሩን ገልጾልናል።

በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የሥራ፣ ሥራ ስምሪት እና ገበያ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሡ ጥላሁን እንደገለጹት፤ አገርን በዘላቂነት ለማበልጸግ የወጣቶችን የፈጠራ ሃሳብ ማበረታታት አስፈላጊ ነው ። ወጣቶቹ ብዙ ውጣ ወረድ አልፈው ሕዝብ የሚጠቅም የፈጠራ ሥራ ማቅረባቸው የሚደነቅ ቢሆንም የፈጠራ ሥራዎችን ተግባራዊ ለማድረግ አሁንም መጣር አለባቸው ።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ብሩህ የሥራ ፈጠራ ሃሳብ ውድድርን በክልሎችም ማስፋፋት የሚያስችል አደረጃጀት መፈጠሩን አመልክተው፤የፈጠራ ሀሳብ አሸናፊዎችን ከማሰልጠን እና መሸለም ባለፈ ክትትል በማድረግና በመደገፍ ሀሳባቸውን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይሠራል ነው ያሉት።

ሀገርና ሕዝብ የሚጠቅሙና ተጨባጭ የሆኑ የፈጠራ ሀሳቦችን ወደ ተግባር ለመለወጥ የፋይናንስ ተቋማት፣ ባንኮች እና አነስተኛ ብድር አቅራቢ ተቋማት ድጋፍ ማድረግ እንደሚኖርባቸው አቶ ንጉሡ ተናግረዋል።

በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የአዳዲስ ሃሳቦች ማበልፀጊያ ዴስክ ኃላፊ ወይዘሮ ዓለምፀሐይ ደርሶልኝ እንዳሉት፤ በሶስት ዙር ለውድድር ከቀረቡት ሃሳቦች መካከል 50ዎቹ ስልጠናቸውን አጠናቀው ውድድር የተካሄደ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ 20ዎቹ ውድድሩን አልፈዋል። ከ20ዎቹ ዳግም ተወዳድረው 15ቱ ሀሳቦች አሸንፈዋል።

ወጣቶቹ ለውድድር ያቀረቧቸው የፈጠራ ሥራዎች የዲጅታል ቴክኖሎጂን ተጠቅመው የተለያዩ ችግሮችን መፍታትና ሕይወትን ማቅለል የሚያስችሉ የፈጠራ ሀሳቦች መሆናቸው ተገልጿል።

በውድድሩ ያሸነፉት የሥራ ፈጠራ ሀሳቦች በአጭር ጊዜ የሚተገበሩ ለብዙ ዜጎች ሥራ የሚፈጥሩና ቶሎ ወደ ገበያ መግባት የሚችሉ መሆናቸውም ተመላክቷል። አሸናፊዎቹ የፈጠራ ሀሳቦች ተግባራዊ ለማድረግ ከአንድ እስከ ሁለት ዓመት የሚፈጁ ሲሆን መሥሪያ ካፒታላቸውም ከግማሽ ሚሊዮን እስከ ሁለት ሚሊዮን የሚደርስ መሆኑ ታውቋል።

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ከዚህ ቀደም በተለያዩ መስኮች አንድ ሺህ 300 የፈጠራ ሀሳቦች አወዳድሮ ያለፉትን 289 የፈጠራ ሀሳቦች መነሻ ካፒታል እንዲያገኙ በማድረግ የፈጠራ ሀሳቦቹ ተተግብረው ሕዝብና ሀገርን የሚጠቅሙበት ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን ተመልክቷል።

# የዘማች ሚሊሻዎች ማሳ በኅብረተሰቡ ተሳትፎ እየታረመ ነው

**ሙሉቀን ታደገ**

ደባርቅ ፦ በሰሜን ጎንደር ዞን ደባርቅ ወረዳ ጎሚያ ቀበሌ የሚገኙ የዘማች ሚሊሻዎች ማሳ በኅብረተሰቡ ተሳትፎ እየታረመ ነው።

በግንባር የሚገኘው የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የጋዜጠኞች ቡድን በደባርቅ ወረዳ ጎሚያ ቀበሌ በመገኘት የዘማች ሚሊሻ ማሳዎች በኅብረተሰቡ ተሳትፎ ሲታረሙ እና እንክብካቤ ሲደረግላቸው ተመልክቷል። በአካባቢው ኅብረተሰቡን ሲያስተባብሩ ያነጋገርናቸው የደባርቅ ወረዳ ሰብል ልማት ቡድን መሪው አቶ አለባቸው ባዘዘ ፤ በወረዳው ለዘማች ሚሊሻ ቤተሰቦች የሚደረገው እንክብካቤ ሁሉን አቀፍ ነው። ለዘማች ሚሊሻ ቤተሰብ የሚሰጠው የምርጥ ዘር እና ማዳበሪያ አቅርቦት በልዩ ሁኔታ እየተካሄደ ነው። የማሳ እንክብካቤውም በግብርና ባለሙያዎች እና በወረዳ አመራሮች እየተመራ በኅብረተሰቡ ተሳትፎ እየተከናወነ ነው ። አሁን በጎሚያ ቀበሌ እየተደረገ ያለው የማሳ ማረም ሥራ ለሁለተኛ ጊዜ መሆኑንም ተናግረዋል።

በደባርቅ ወረዳ ስር 33 ቀበሌዎች እንደሚገኙ የተናገሩት አቶ አለባቸው ፤ በእነዚህ ቀበሌዎችም ከአንድ ሺ አምስት መቶ በላይ ሚሊሻዎች ወደ ጦር ግንባር መዝመታቸውን ገልጸዋል ። ከእነዚህ መካከል 75ቱ በጎሚያ ቀበሌ መሆናቸውን ገልጸዋል። በወረዳው የዘመቱት የአንድ ሺ አምስት መቶ ሚሊሻዎች ማሳ ከ705 ሄክታር በላይ መሬት እንደሚሸፍን የገለጹት አቶ አለባቸው ፤ ኢትዮጵያውያን በሰላሙ ጊዜ አራሽ፤ ሀገር በወራሪዎች በተደፈረች ጊዜ ደግሞ ተኳሽ መሆናቸውን ማሳያ መሆኑን ጠቁመዋል።

ኅብረተሰቡ ለዘማች ሚሊሻው አረም የማረም ሥራ ብቻ አይሠራም ያሉት አቶ አለባቸው ፤ ከእርሻ ማረስ ጀምሮ እህሉ ወደ ጎተራ እስከሚገባበት ባሉት ጊዜ የሚከናወኑ ማናቸውንም ተግባራት በኅብረተሰቡ ተሳትፎ እንደሚከናወኑ ጠቁመዋል።



**አቶ አለባቸው ባዘዘ**



**አቶ አለምነው መንግስቴ**



የዘማች ሚሊሻ ማሳ ሲያርም ያገኘነው የጎሚያ ቀበሌ ነዋሪው አርሶ አደር አለምነው መንግስቴ በበከላቸው፤ ዘማች ሚሊሻዎች የሽብር ቡድኑ ትሕነግ ሴቶችን እንዳይደፍር፣ ሕጻናት እና አረጋውያን ለስደት እንዳይዳርግ ፣ የግል እና የመንግሥት ንብረቶችን እንዳያወድም ለማድረግ ግንባር ላይ መስዋዕትነትን እየከፈሉ ይገኛል። ይህን ለሚያደርጉ ዘማች ሚሊሻዎች በኅብረተሰቡ ተሳትፎ ማሳቸውን ማረም ከኅብረተሰቡ የሚጠበቀው ዝቅተኛው አስተዋጽዖ ነው ብለዋል።

በጎሚያ ቀበሌ የሚገኘው አርሶ አደር ለዘማች ሚሊሻዎች ማሳቸውን ከመንከባከብ ባለፈ ለቤተሰባቸውም ሁሉን አቀፍ ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ የተናገሩት አቶ አለምነው ፤ ሰርጎ ገቦችን ከመጠበቅ እና ግንባር ለሚገኘው ሠራዊት የሎጅስቲክስ ድጋፍ በማድረግ ረገድ የተለያዩ ሥራዎች መሥራታቸውን አመላክተዋል።

የዘማች ሚሊሻ ልጅ የሆነው ወጣት አበበ ጀጀው እንደተናገረው ፤ አባቱ አስር አለቃ ጀጀው ኃይሉ የሽብር ቡድኑ ትሕነግ የአማራ ክልልን በወረረበት ጊዜ የክልሉ መንግሥት የጠራውን የክተት አዋጅ ተከትሎ ሐምሌ 27 ቀን 2013 ዓ.ም ወደ ግንባር አቅንቷል። በጭና ፣ በዛሪማ እና አሁን ደግሞ በአዲአርቃይ በነበረው ውጊያ ተሳትፎ የሽብር ቡድኑን ድል ማድረጉንና በዚህም በአባቱ ጀግንነት ከፍተኛ ኩራት እንደተሰማው ይናገራል።

የጎሚያ ቀበሌ ነዋሪዎች በአረም ፣ በሰብል መሰብሰብ ፣ በእርሻው እና እህሉ ተሰብስቦ ወደ ጎተራ እስኪገባ ድረስ እያደረጉላቸው ለሚገኘው ሁለንተናዊ ድጋፍ አባታችን በቤት ያለ ያህል እንዲሰማን ያደረገ ነው ያለው ወጣት አበበ ፤ በዚህም የጎሚያ ቀበሌ ነዋሪዎችን እና ድጋፉን እያስተባበሩ የሚገኙትን የግብርና ባለሙያዎች እንዲሁም የወረዳውን አመራሮች አመስግኗል።

ዜና



ፎቶ - ዳኜ አበራ

## ‹‹የመስቀል በዓልን ስናከብር ኢትዮጵያውያን በሰላምና በመተሳሰብ እንዲኖሩ የምናደርገውን ጥረት ሳናቋርጥ ሊሆን ይገባል››

- ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ
የሰሜን ወሎ ዞን ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

ወልድያ፡- የመስቀል በዓልን ስናከብር ኢትዮጵያውያን በሰላምና በመተሳሰብ እንዲኖሩ የምናደርገውን ጥረት ሳናቋርጥ ሊሆን ይገባል ሲሉ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሰሜን ወሎ ዞን ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ ተናገሩ።

በሃገር ውስጥና በውጭ ለሚገኙ ሕዝበ ክርስቲያኖች ለ2015 ዓ.ም የመስቀል በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልካም ምኞት መግለጫ አስተላልፈዋል።

ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ ትናንትና መግለጫውን ሲሰጡ፤ የመስቀል በዓልን ስናስብ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰላምና በመተሳሰብ እንዲኖሩ የምናደርገውን ጥረት ሳናቋርጥ ሊሆን ይገባል ብለዋል።

ይቅር ባይነት ከራስ ይልቅ ለሌሎች ማሰብን የሚጠይቅ በመሆኑ አገራችን ኢትዮጵያ ሰላም እንድትሆን ዕርቅን ትጠብቃለች ሲሉ ተናግረዋል።

ምንም በማያውቀው ሁኔታ በመከራ ውስጥ የወደቀውና የሚሰቃየው ሕዝብ ሰላምን ይፈልጋል ያሉት ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ ፤ ሕዝቡ እየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ የሰበከውን ይቅርባይነትና ሰላምን አግኝቶ መኖር እንደሚሻ አስረድተዋል።

እንደ ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ፤ በመስቀሉ የተገኘው ሰላምና ይቅርባይነትን ነው። እየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖም የሰቀሉትን አካላት አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ነው ያለው።

ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ አጠገቡ የተሰቀለውን ወንበዴ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትኖራለህ የሚል የምስራች የነገረበት የምህረት ቀን ነው። በመሆኑም በዓሉን ስናስብ ግጭትንና መከራን ሳይሆን ድህነትን መፈለግ ይገባናል ብለዋል።

ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በተለይም ለእርስ በእርስ መጠፋፋት ምክንያት የሆነ ወገኖች ልብ ልንገዛ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ዓለም ሁሉ ከሚጠፋ ሰው እራሱን እንደክርስቶስ አሳልፎ ቢሰጥ ሌላውን ማዳን ይችላል ያሉት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ፤ ለእርስ በእርስ መጠፋፋት ምክንያት የሆኑ ወገኖቻችን ሌላውን ለማዳን እራሳቸውን በይቅር ባይነት ሊገዙ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ለእርስ በእርስ ግጭቶች ምክንያት የሆኑ ወገኖች ስለሰላም ልናስብና በመከራ ውስጥ የወደቀውን ሕዝብ ልናሳርፈው ይገባል ብለዋል።

የእራስን ጥቅም ለማስቀደም ሌሎችን ለጥፋት የምናስቀድምበት ጊዜ እንዲያበቃ በቅድስት ቤተክርስቲያን ስም አሳስባለሁ ሲሉ ተናግረዋል።

በዓሉን ስናከብር የተቸገሩትንና በመከራ ላይ ያሉትን ሰዎች ልናስብ ይገባል ያሉት ሊቀ ጳጳስ አቡነ ኤርምያስ፤ የመስቀሉ ሰላም በኢትዮጵያና በሕዝቦቿ ላይ ይብዛ፤ መልካም የስቅለት በዓል ይሁንልን ብለዋል።

በሰሜን ወሎ ዞን ወልዲያ ከተማ በትናንትናው ዕለት የደመራ በዓል በደማቅ ሁኔታ የተከበረ ሲሆን፤ የሰሜን ወሎ ዞን ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ኤርምያስ የደመራውን ሥነሥርዓት አስጀምረዋል።

በአሸባሪው ትህነግ ወረራ ምክንያት በ2014 ዓ.ም የደመራ በዓል በወልዲያና አካባቢው በደማቅ ሁኔታ አለመከበሩ የሚታወስ ነው።

# ኢትዮጵያውያን በመስቀል ደመራ በዓል ያሳዩትን አንድነት ሊያጠናክሩ እንደሚገባ የእምነቱ ተከታዮች ገለጹ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያውያን በመስቀል ደመራ በዓል ያሳዩትን የመከባበር፣ የመተማመን፣ የፍቅር፣ የአንድነት እና የመተሳሰብ ባህልን ሊያጠናክሩ እና ወላጆች ልጆቻቸውን በመልካም መክረው ሊያሳድጉ እንደሚገባ የክርስትና እምነት ተከታዮች ገለጹ።

የ2015 ዓ.ም የመስቀል ደመራ በዓል ትናንት በመስቀል አደባባይ በድምቀት ተከብሯል። በበዓሉ የታደሙት አባ ተስፋ ስላሴ ወልደማርያም፤ ወላጆች ልጆቻቸውን በመልካም መክረው፣ ፈሪሃ እግዚአብሄር እንዲያድርባቸው፣ታላላቆቻቸውን የሚያከብሩ እንዲሆኑ ሊያስተምሯቸው ይገባል ብለዋል።

ትውልዱ ከመስቀል ደመራ በዓል መፋቀር፣ መከባበርን መማር እንዳለበትም ነው የተናገሩት። ‹‹መስቀል ሰላም ማለት ነው። ሰላምን የምናስታውስበት፣የምንሰብክበት፣ ትዕግስትን የምንማርበት ነው›› ብለዋል። እርስ በእርስ በመፈቃቀር፣ ትዕዛዛቱን በመፈጸምና በተግባቦት መኖር እንደሚገባም አባ ተስፋ ስላሴ አመልክተዋል።

‹‹ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ውጭ በመሆናችን፣ ግለኝነት በመሰልጠኑ፣ አብሮነት በመጥፋቱ አሁን ለተፈጠረው ችግር ምክንያት ሆኗል›› በማለት ጠቁመው፤ አብሮነት ከጠፋ መራራቅ ይፈጠራል፣ በመራራቅ ውስጥም መጨካከን አለ እነዚህን በማስወገድ እርስ በእርስ መዋደድ ያስፈልጋል ብለዋል።

የበዓሉ ታዳሚ መምህር መክብብ ገብረማርያም በበኩላቸው፤ ይህ ቱባ ባሕል እንዳይጠፋና እንዳይበረዝ የኢትዮጵያ ነገሥታት፣ የሃይማኖት አባቶች መስዋዕትነት ከፍለው ጠብቀው ለትውልድ ያስተላለፉት መሆኑን አስታውሰዋል።

በዓሉ ለዓለም፣ ለአፍሪካውያንና ለኢትዮጵያውያን ብርሃን እና ክብር መሆኑን ነው የገለጹት። የሰው ልጆች ወካይ ቅርስ ሆኖ መመዝገቡ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለውም ጠቁመዋል። ይህ ወቅት ብርሃን የሚታይበት፣ አዕዋፋት የሚያዜሙበት፣ ጫካ ውስጥ የቆዩ እንስሳት የሚወጡበት፣ የሰው ልጆች እርስ በእርስ የሚገናኙበት፣ እርቅ የሚፈጸምበት የትውልድ መደሰቻ በዓል መሆኑንም ተናግረዋል።

ደመራው የሰላምና የአንድነት ምሳሌ ነው። በዓሉ አንድነትን ያሳያል፣ ይህ ደግሞ ለአፍሪካውያንና ለዓለም ምሳሌ የሚያደርግ መሆኑን ነው መምህር መክብብ የገለጹት። ኢትዮጵያ የሰላም፣ የአንድነት እና የፍቅር ምሳሌ ናት። ይህ አንድነት ደግሞ የሚገለጸው በደመራው ብርሃን ነው ብለዋል። በበዓሉ ወቅትም አባቶች ተሰብስበው ለዓለም ሰላም መስፈን ጸሎት የሚያደርጉበት እንደመሆኑ ሕዝቡ የሰላም አምባሳደር መሆን አለበት ሲሉ ጥሪ አቀርበዋል።


ወይዘሮ ማርታ ተስፋዬ በበኩላቸው፤ የሰንበት ተማሪዎቹ በሙሉ ዝማሬና ወረብ በማቅረብ በዓሉን በድምቀት ማክበራቸውን ጠቁመዋል። በርካታ የእምነቱ ተከታዮችም ሆኑ ሌሎችም በአንድነት ተሰባስበው በመተማመንና በመከባበር የሚያከብሩት፣ የእርስ በእርስ ግንኙነትን የሚያጠናክር የአንድነት በዓል መሆኑንም ነው የገለጹት።

የመስቀል ደመራ በዓልም ሆነ ጥምቀትና ሌሎች የአደባባይ በዓላት ከሃይማኖታዊ በዓልነታቸው ባሻገር በዩኔስኮ የተመዘገቡ በመሆኑ ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ ደረጃ እንድትታወቅ እንደሚያግዝ፣ የቱሪስት መዳረሻ እንድትሆን በማድረግ የገቢ ምንጭ እንደሚፈጥርም ተናግረዋል።



ፎቶ - ሀዱሽ አብርሃ

አባ ተስፋ ስላሴ ወልደማርያም፤



ወይዘሮ ማርታ ተስፋዬ



ፎቶ - ሀዱሽ አብርሃ

# ‹‹ባህላዊና ሃይማኖታዊ እሴቶቻችን የአንድነታችን ማሳያዎች ናቸው››

- የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ ፡- ባህላዊና ሃይማኖታዊ እሴቶቻችን የአንድነታችን ማሳያዎች መሆናቸውን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ።

አገልግሎቱ ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች ለደመራ እና የመስቀል በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፏል።

የመስቀል በዓል በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች በደማቅ ከሚከበሩ በዓላት አንዱ ነው ያለው አገልግሎቱ፤ ከባህላዊና ኃይማኖታዊ ክንዋኔነቱ አልፎ ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ ከምትታወቅባቸው የማይዳሰሱ ቅርሶች መካከል አንዱ መሆኑንም ገልጿል።

የመስቀል በዓል በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ተቋም (ዩኔስኮ) የማይዳሰስ ቅርስ ተደርጎ በመመዝገቡ ከሀገር አልፎ የዓለም ቅርስ በመሆን ሀገራችን በዓለም አቀፍ መድረክ የምትታወቅበት ሃብታችን ሆኗልም ነው ያለው መግለጫው።

በሀገር አቀፍ ደረጃም የመስቀል በዓል ብሔር ብሔረሰቦችን ከሚያስተሳስሩ ቱባ እሴቶቻችን መካከል ቀዳሚ ስፍራን እንደሚይዝም አውስቷል።

የመስቀልና የደመራ አከባበር ሥነሥርዓት በሁሉም የሀገራችን ክፍሎች የሚከበር ታላቅ ባህላዊና ኃይማኖታዊ ክዋኔ በመሆኑ በዓሉ ማኅበራዊ ትስስርን የሚያጠናክር እንዲሁም የአንድነትና የመቻቻል በዓል መሆኑንም ነው ያነሳው።

በዓሉ ጭጋጋማው የክረምት ወቅት አልፎ በክረምት ወቅት የተራራቁ ቤተሰቦች የሚገናኙበት ወቅት በመሆኑ የመስቀልን በዓል ከሌላው ጊዜ በተለየ ተናፋቂ እንደሚያደርገውም አንስቷል።

በተጨማሪም በዓሉ እንደየብሔሩና አካባቢው ቋንቋ በተለያዩ ስያሜዎች የሚታወቅ ቢሆንም በየአካባቢው በልዩ መገለጫ የሚከበር በመሆኑ ኢትዮጵያውያን በብዙ ባህላዊ እሴቶች የተጋመዱ ስለመሆናቸው ትልቅ ማሳያ መሆኑንም ነው የገለጸው።

# አገልግሎቱ በሕገ-ወጥ የገንዘብ ማስተላለፍ ተግባር ላይ የተሠማሩ አካላት ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ አሳሰበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በሕገ-ወጥ የገንዘብ ማስተላለፍ ተግባር ላይ የተሠማሩ አካላት ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ የኢፌዴሪ የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት አሳሰበ።

የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ጉዳዩን አስመልክቶ ባወጣው መግለጫ፤ አንዳንድ አካላት በሕጋዊ የገንዘብ ማስተላለፍ (ሕጋዊ ሐዋላ) ሽፋን ገንዘብ የማስተላለፍ ድርጊት እየፈጸሙ እንደሚገኙ አስታውቋል። ይህም ኢትዮጵያ ከተለያዩ ምንጮች ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ ማሳጣት ብሎም የውጭ ምንዛሪውን በውጭ ሀገራት የማስቀረት የፋይናንስ ወንጀል ድርጊት መፈፀም መሆኑን አስረድቷል።

ተቀማጭነታቸውን ከኢትዮጵያ ውጭ በማድረግ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሆኑ ግብረአበሮቻቸው ጋር በመመሳጠር በሕጋዊ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ መግባት የሚገባውን የውጭ ምንዛሪ በውጭ ሀገራት በማስቀረት ክፍያውን በኢትዮጵያ ብር የሚፈፅሙ መሆናቸውም ተመላክቷል።

በተለይም ‘አዶሊስ’ ፣ ‘ሸጌ’፣ ሠላም ፣ ሬድ ሲ የተባሉና በውጭ ሀገር በገንዘብ ማስተላለፍ ተግባር ላይ የተሠማሩት አካላት በሕጋዊ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ መግባት የነበረበትን የውጭ ምንዛሪ ለኢትዮጵያ ባንኮች የላኩ በማስመሰል ሀሰተኛ ደረሰኝ ጭምር በማዘጋጀትና በመጠቀም የውጭ ምንዛሪውን በውጭ ሀገራት በማስቀረት በኢትዮጵያ ውስጥ የውጭ ሀገራት ገንዘብ ምንዛሪና የኑሮ ውድነት እንዲባባስ በማድረግ ላይ ናቸው ብሏል አገልግሎቱ።

እነዚህ የገንዘብ አስተላላፊዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ግብረ አበሮቻቸው ከሆኑ ከ600 በላይ የሂሳብ ምንጮች በብር ክፍያ ሲፈፅሙ እንደነበር መግለጹንም ከአገልግሎቱ የተገኘው መረጃ ያመላክታል።

እነዚህ አካላት ወደ ኢትዮጵያ በሕጋዊ መንገድ




መግባት የነበረበት ገንዘብ የኮንትሮባንድ ንግድን ጨምሮ ለተለያዩ የወንጀል ድርጊቶች መፈፀሚያ እንዲውል በማድረግና በኢትዮጵያ የፋይናንስ ሥርዓት ላይ ጉዳት እያደረሱ መሆናቸውም ተጠቁሟል።

የኢፌዲሪ ፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት፤ ሕገወጥ የገንዘብ ማስተላለፍ ተግባርን ጨምሮ መሰል የፋይናንስ ወንጀሎች የሚፈፅሙ አካላትንና በድርጊቱ የተሳተፉ ግብረ አበሮቻቸውን በሕግ ተጠያቂ ለማድረግ ከሀገር ውስጥ ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ከውጭ ሀገራት አጋር ተቋማት ጋር በማካሄድ ላይ ያለውን ሥራ አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቋል።

በዚህም አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የወንጀል ድርጊቱ ተዋናይና ተባባሪ የሆኑ አካላት ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ አገልግሎቱ አሳስቧል።

# ‹‹ከጥላቻ ፍቅርን፣ ከመገፋፋት ወንድማማችነትን ከመስቀሉ በመማር አብሮነትን ልናስቀጥል ይገባል››

- ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡ -እንደ አገር ከጥላቻ ፍቅርን፣ ከመገፋፋት ወንድማማችነትን፣ከራስ አልፎ ለሌሎች ማሰብን በማስቀደም ከመስቀሉ በመማር አብሮነትን ማስቀጠል ይገባል ሲሉ ከንቲበ አዳነች አቤቤ አመለከቱ።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የመስቀል ደመራ በዓል ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት መልዕክት፤ኢየሱስ ክርስቶስ በዘር፣በቀለምና በሃይማኖት ሳይለያይ ለሰው ልጆች ሁሉ ኃጥያት ስርየት በመስቀል ላይ ሞቶ እውነተኛ ፍቅሩን ገልጿል። በተቃራኒው ዛሬ በዓለም ፍቅር ጎድሎ ራስ ወዳድነት በመፋፋሙ ምክንያት የሰው ልጅ የብዙ ፈተናዎች ሰለባ ለመሆን ተገድዷል።

በመሆኑም እንደ ሀገር ለእኛ የሚበጀን ከጥላቻ ፍቅርን፣ ከመገፋፋት ወንድማማችነትን፣ ከራስ አልፎ ለሌሎች ማሰብን በማስቀደም ከመስቀሉ እየተማርን በአብሮነት መቀጠል ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ ሀገራችን ኢትዮጵያም ከእያንዳንዱ ልጇ መተዛዘንና መተሳሰብን በጽኑ እንደምትፈልግ ጠቁመዋል።

እንደ ወይዘሮ አዳነች ገለጻ፤ የመስቀል ደመራ በዓል በዩኔስኮ በመመዝገቡ ኢትዮጵያን በዓለም ከማስተዋወቅ ባሻገር አዲስ አበባም የቱሪስት መዳረሻ ከተማ እንድትሆን ከፍተኛ ሚና መጫወቱን ገልጸዋል። የሀገሪቱን ሕዝቦች በማስተሳሰርና በማቀራረብ ረገድም የመስቀል በዓል ሚናው የጎላ መሆኑን ተናግረዋል።

ዛሬ በኢትዮጵያ ላይ የሚታየው ነባራዊ ሁኔታ መስቀሉን ለመደበቅ የተሠራ ሴራ ጋር በእጅጉ እንደሚመሳሰል የተናገሩት ወይዘሮ አዳነች፤ በፍቅር ፈንታ ጥላቻ ፣ በሀቅ ላይ ሐሰት የተከመረበትና የተመከረበት፣ የተፈጥሮ ሀብቷን እንዳትጠቀም የወረደባት የክስ ውርጅብኝ የሚያሳየው የመስቀሉ ክስተት ዋጋ መክፈል ብቻ ሳይሆን እውነት የሚገለጥበት ክስተት በመሆኑ የኢትዮጵያ እውነትም እንደሚገለጥ ማሳያ እንደሆነ አስገንዝበዋል።



በመሆኑም ኢትዮጵያ እውነቷ፣ ብሔራዊ ጥቅሟና ሉዓላዊነቷን ለማስከበር ውድ ሕይወታቸውን የማይሰስቱ ልጆች ያሏትና በኪዳን የጸናች አገር መሆኗን ያነሱት ከንቲባዋ፣ ይህቺ ጽኑ አገር የሚያጋጥሟትን ፈተናዎች በድል ተወጥታ ሕልውናዋን እንደምታስቀጥል ምንም ጥርጥር አይኖርም ብለዋል።

መስቀል የሰላም፣ የፍቅርና የአብሮነት ተምሳሌት ሲሆን የመስቀል ደመራ በዓል ደግሞ ጨለማው በብርሃን የመሸነፍ ማሳያ ነው ያሉት ወይዘሮ አዳነች፤ በመሆኑም በዓሉ ሲከበር በፍቅር፣ በመተሳሰብና ለዘላቂ ሰላም መረጋገጥ እየሠራን፣ ጀግኖቻችን እያከበርንና ደጀንነታችን እያሳየን ጨለማ በሆኑብን ላይ እንደ ደመራ አንድ ሆነን በአሸናፊነት ብርሃናችን እያበራን ሊሆን ይገባል ብለዋል።

መንግሥት ከሁሉም ሃይማኖት ጋር እንደሚሠራ የገለጹት ወይዘሮ አዳነች፤ አንጋፋና ብዙ የሀገሪቱ ቅርሶች ጠብቃ ካቆየችው ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጋርም በሰላም፣ በልማትና በሀገራዊ ጥቅሞች ዙሪያ በጋራ ለመሥራት ቁርጠኝ መሆኑን አስታውቀዋል።

# ጠብን በእርቅ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ከእልኸኝነት ወጥተን የእግዚአብሔርን ድምጽ በመስማትና ተግባራዊ በማድረግ በሰላምና አንድነት በመተባበርና በመተጋገዝ፣ በመረዳዳትና በመቻቻል መኖር እንደሚገባ ጠቅሰው፤ እግዚአብሔር ለሀገራችን ሰላምንና ፍቅርን እንዲሰጠን ሁላችንም በርትተን ልንጸልይ ይገባልም ብለዋል።

የባህልና ስፖርት ሚኒስትሩ አቶ ቀጄላ መርዳሳ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የመስቀል ደመራ በዓል ለሕዝቦች መቀራረብ የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው።

በዓሉ አያቶቻችንና ቅድመ አያቶቻችን እንዳስተላለፉልን ከጨለማው ወደ ብርሃን መሸጋገራችንን አመላካች ተደርጎ እንደሚወሰድ ጠቁመው፤ በዓሉ የጥል ግድግዳ ፈርሶ የዕርቅ ሥርዓት የሚከናወንበት ታላቅ በዓል መሆኑንም አመልክተዋል።

የመስቀል በዓል በመላ ሀገሪቱ በተመሳሳይ ሰዓት በጋራ የሚከበር እንደመሆኑ መስቀል የሁሉም የጋራ ዕሴት መሆኑን አውስተው፤ ይህ አኩሪ እሴት በሌሎች የዓለም ሀገራት በብዛት የማይስተዋል በመሆኑ ጎብኚዎችን በመሳብ በኩል ሚናው ትልቅ ነው።

በመሆኑም መስቀልን የመሰሉ ሃይማኖታዊና ባህላዊ እሴቶች በሚገባ ተጠንተው በአግባቡ እንድንጠቀምባቸውና ከነክብራቸው ለትውልድ እንዲተላለፉ ለማድረግ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በትኩረት እንደሚሠራ ጠቁመዋል።

የ2015 ዓ.ም የመስቀል ደመራ በዓል በአዲስ አበባ መስቀል አደባባይ የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ፣ ሊቃነ ጳጳሳት፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ ሚኒስትሮችና ሌሎችም ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች፣ የሃይማኖት ተቋማት ተወካዮች፣ ዲፕሎማቶች፣ የውጭ አገር ጎብኝዎችና በርካታ ቁጥር ያላቸው የእምነቱ ተከታዮች በተገኙበት በድምቀት ተከብሯል።

የመስቀል ደመራ በዓል በዓለም ካሉ የማይዳሰሱ ቅርሶች አንዱ ሆኖ በዩኔስኮ መመዝገቡ ይታወቃል።

# ‹‹የመስቀል በዓል...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ብርዱ በሙቀት፤ ድብርቱ በተስፋ ይተካል። አስቸጋሪውንና ፈታኙን ወቅት መሻገሩን ደመራው ያበሥራል ብለዋል። “መነሻው የአንድነታችን፤ የአከባበሩ ልዩ ልዩ መሆን ደግሞ የኅብራዊነታችን ማሳያ ነው” ሲሉም በመልዕክታቸው አንስተዋል።

የመስቀል በዓል ያለፈውን ፈተና የምናስወግድበትና ለመጪው ጊዜ ተስፋ የምንሰንቅበት ነው። የአከባበሩ ሥነ ሥርዓትና የሸማግሌዎች ምርቃት ይሄንን ያሳየናል። ኢትዮጵያም በዚህ ዓመት የከረሙ ችግሮቿን ፈትታ ወደ አለመችው የብልጽግና ጉዞ እንደምትሄድ ሁላችንም ልናውቅ ይገባል ብለዋል።

ኢትዮጵያ አስቸጋሪና ፈታኝ ጊዜን አልፋ እዚህ ደርሳለች። ከድጡ ወደ ማጡ እንድትወርድ ያልተሠራ ሴራ የለም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ “ስለ በረሃማነት እየተሟረተብን ሀገራችን አረንጓዴ ለበሰች፤ ስለ ኪሣራ እየተለፈለፈ ኢኮኖሚያችን ፈተናዎቹን እየተሻገረ ቀጠለ፤ ከግራ ከቀኝ እየተዋከብን ሦስተኛውን ዙር የህዳሴ ግድብ ሞልተን ኃይል አመንጭተናል” ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመልዕክታቸው፤ ስለ ኢትዮጵያ መጥፎ ነገሮች ሲወሩ የሕዝቦቿ አንድነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እንደ ብረት እየጠነከረ መጥቷል። የትም አይደርሱም የተባሉ ፕሮጀክቶች ለመጠናቀቅ በቅተዋል። ይህ ሁሉ አልሳካ ሲል ደግሞ ትዕግሥት እንደ ፍርሃት፣ ሰላም ፈላጊነት እንደ ድክመት ተቆጥሮ ለሦስተኛ ጊዜ በሀገራችን ላይ ጥቃት ተፈጽሟል ብለዋል።

ኢትዮጵያን ለመታደግ፣ ሕዝብን ከብተና ለማዳን እና ሀገር እንደ ሀገር ቀጥላ ለትውልድ ሉዓላዊነት ኢትዮጵያን ለማስረከብ መከላከልን አማራጭ አድርገን ወስደናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ አሁን እያደረግን ያለነው የመከላከል ውጊያ ይኼንን ታሪካዊ አደራ ለመወጣትና ብሔራዊ ጥቅምን ከአደጋ ለመከላከል ያሰበ ነው ብለዋል።

የእኛን ጥረት በተገቢ መንገድ የሚያወድስና የሌላኛው ወገን እምቢታ በተገቢው ልክ የሚያወግዝ ግን ጥቂት ነው። ለሰላም የተዘረጉ እጆች ሰላምን የሚመርጡት ጦር ለመያዝ ስለማይችሉ አይደለም፤ ሰላምን ስለሚመርጡ ብቻ ነው። ለሰላም የዘረጋነው እጅ ምንም ዋጋ ስላላገኘ ጦር እንዲይዝ እየተገደደ ነውም ብለዋል በመልዕክታቸው።

የሞላው ወንዝ ይጎድላል፤ ፈታኙ ጭቃ ይደርቃል፤ ጥሻው ይገለጣል፤ ጨለማውም ይበራል፤ ብርዱ ይቀላል፤ ሜዳና ተራራው በአበባ ያጌጣል። በዚህ ወቅት ነው ተሠውሮ የኖረው መስቀል የተገኘው። ስለዚህ የኢትዮጵያን ጥንካሬን ከሚያሳዩን ወቅቶች አንዱ የመስከረም ወር እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል ሲሉም ገልጸዋል።

ደመራው፣ ችቦው፣ የወጣትና የልጆች ፌሽታ፣ ለሽማግሌዎች የሚሰጠው ቦታ፣ ምርቃቱ፣ መልካም ምኞቱ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ ተመሳስሎና ተቀራርቦ ሲከበር ስናይ ኢትዮጵያ የተሣሠረችበትን ውስጣዊ ሥር እንድንመረምር ያደርገናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በመልዕክታቸው፤ ይህ እንደ እንግዳ ደራሽ፣ እንደ ውኃ ፈሳሽ በድንገት የሆነ አይደለም። መነሻው አንዳች የጋራ ዕሳቤ ያለው ነው ብለዋል።

መነሻው የአንድነታችን፤ የአከባበሩ ልዩ ልዩ መሆን ደግሞ የኅብራዊነታችን ማሳያ እንደሆነም ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በዚህ ዓመት በሁለት እጆቿ እየሠራች ፈተናዋን ትሻገረዋለች። በአንድ እጇ ብሔራዊ ጥቅሟን በሚገባ አስጠብቃ ችግሯን ለመጨረሻ ጊዜ ለመፍታት ትታገላለች። በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝቡ በወዙ ጎተራው እንዲሞላ፤ ምሳው በብድር ሳይሆን ከራሱ ማሳ ዘግኖ እንዲመገብ የሚችልበትን ስትራቴጂ ነድፈን መንቀሳቀስ እንጀምራለን ብለዋል።

አሁን ያለንበት ዘመን በአነስተኛ ቦታዎች ቀላል ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም በምግብ ራሳችን ለመቻል የሚያስችሉ ዕድሎች የተፈጠሩበት ዘመን ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ፣ ታላላቅ የእርሻ መሬት የሌላቸው ሀገሮች በዚህ ውጤታማ ናቸው። ስለዚህ ይህ ውጤት በኛም እንዲደገም ሁሉም ኢትዮጵያዊ የበኩሉን ሊወጣ ይገባል ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

ይህ ጉዟችን “የሌማት ትሩፋት” ይባላል። ዓላማው በቀላል መንገድ ገበታችንን በተመጣጠነ ምግብ መሙላት ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ኢትዮጵያ የገጠማትን መከራ አልፋ ለዚህ ክብረ በዓል በመድረሷ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንኳን አደረሳችሁ ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በዓላትን የሰላም፣ የፍቅርና አብሮነት መገለጫ እናድርጋቸው!

ወርሃ መስከረም ለኢትዮጵያውያን የወር መጀመሪያ ብቻ ሳይሆን፤ የማንነታቸውን እሴት ከፍ አድርጎ የመግለጽ አቅም ያለው የበዙ በዓላትን በጉያው ያቀፈ ታላቅ ወር ነው፡፡ የመስከረም ታላቅ ወርነት የሚጀመረው ቀደምት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ዘመን ቀምረው ለኢትዮጵያ የራሷን ዓመት መቁጠሪያ ሲያበረክቱላት፤ የዓመቱ መጀመሪያ የወራት ራስ አድርገው ሲመርጡት ጀምሮ ነው፡፡ ይህ ያለምክንያት አልነበረም፡፡ ይልቁንም መስከረም የአዲስ ተስፋ ጅማሮ፣ የጨለማ ዘመን ማብቂያ፣ የአስፈሪ ነገሮች ሁሉ መወገጃ፣ በጥቅሉ የብርሃን ዘመን መባቻ በመሆኑ እንጂ፡፡ እናም ኢትዮጵያውያን አዲሱን ዓመት በዚህ የብርሃን መባቻ ላይ አንድ ብሎ እንዲጀመር ይሁነኝ ብለው የመረጡት የብርሃንና የሰላም ብስራት ወር በመሆኑ ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን የጋራ የዘመን ቀመራቸው አድርገው በመስከረም የመጀመሪያው ዕለት አንድ ብለው አዲስ ዓመትን ሲጀምሩ፤ ምድራቸው በአበባ ደምቃ የምትታይበት ወቅት እንደመሆኑም እንቁጣጣሽ ብለው እለቷን በመሰየም ራሳቸውን ከምድራቸው ድምቀት ጋር አወዳጅተው የዘመኑ ያማረ እንዲሆንላቸው ተመኝተው ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን በዚህ መልኩ የጋራ ዘመናቸውን ይጀምሩ እንጂ እንደ መስቀል ፣ ጊፋታ፣ ዮ...ማስቃላ፣ ያሆዴ እና ኢሬቻን የመሳሰሉ የዚሁ የአዲስ ዘመንን ብስራት፣ የጨለማው ዘመን አልፎ የብርሃንን መምጣት፣... የሚያበስሩ አያሌ ባህልና ትውፊት ያላቸውና በጋራ ደምቀው የሚያከብሩ ድንቅ ሕዝቦች መሆናቸውንም በዘመናት ጉዟቸው አረጋግጠዋል፡፡ ዛሬም ድረስ እነዚህ በዓላት የሰላም፣ የባህል እንዲሁም አጠቃላይ የኢትዮጵያውያን ማንነትና አብሮነት መሰረታቸው ማጽኛ ስለመሆናቸው ለዓለም ሕዝብ እያረጋገጡ ይገኛል፡፡

አዲስ ዓመትን ሲጀምሩ ዘመኑን የሰላምና የፍቅር፣ የመተሳሰብና የአብሮነት፣ የይቅርታና የስኬት፤... እንዲሆንላቸው ተመኝተው ነው፡፡ ይሄ ምኞትና ፍላጎታቸው ደግሞ ከቃል ባለፈ በበዓላቶቻቸው ላይ በተግባር እየገለጡ የሚኖሩት ስለመሆኑ የሚያረጋግጡት ነው፡፡ በሃዲያ፣ በወላይታ፣ በጋሞና ሌሎችም ሕዝቦች የዘመን መለወጫ በዓላት የተስተዋለውም ይሄው የበዓላቱ የማንነትና የባህል መገለጫ ብቻ ሳይሆኑ፤ የሰላማቸው መሰረት፣ የአብሮነታቸው አውድ፣ የትብብራቸው ሰገነት ስለመሆናቸው ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር እነዚህ በዓላት ለሃዲያ፣ ለወላይታ፣ ለጋሞና በውስጣቸው ላሉ ሕዝቦች ብቻ ሳይሆን፤ ለመላው ኢትዮጵያውያን፤ ከፍ ሲልም ለመላው ዓለም የአብሮነትና ትብብርን ምንነት አደባባይ ወጥተው የመሰከሩና ትምህርት የሰጡ፤ በዚህ አስተምህሯቸውም በዓለም ቅርስነት ተጠብቀው ሊያዙ የሚገባቸው ስለመሆኑም የመሰከሩ ናቸው፡፡

በዚህ መሰል ከፍ ያለ እሴትና ትውፊቱ የዓለም ቅርስ ሆኖ የተመዘገበውና ዓለም በየዓመቱ በጉጉት የሚጠብቀው የመስቀል በተለይም የደመራ በዓል አንዱ ነው፡፡ ይህ በዓል ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በባለቤትነት ይዛ የአደባባይ በዓል አድርጋ የምታዘጋጀው ይሁን እንጂ፤ በዓሉ የመላው ኢትዮጵያውያን የአብሮነት፣ የመተባበር፣ የሰላም እሴት መገለጫ፤ ከዚህም አልፎ የዓለም ሕዝብ ሀብት የሆነ በዓል ነው፡፡ ትናንት የደመራው በዓል በመስቀል አደባባይ በደመቀና የኢትዮጵያውያንን የሰላም፣ የአብሮነትና የመተባበር ከፍ የለ ሰብዕና ማሳያ ሆኖ ሲከበር የታየውም ይሄው እውነት ነው፡፡

በዓሉን ለማድመቅ በዋዜማው የከተማ አስተዳደሩ ከፍተኛ አመራሮች ጨምሮ፤ የተለያዩ እምነት ተከታይ አባቶችና ምዕመናን በአደባባዩ ተገኝተው የጽዳት መርሃ ግብር ማዘጋጀታቸው በኢትዮጵያውያን ዘንድ ሃይማኖታዊ በዓላትም ሆኑ ባህላዊ መሰረት ያላቸው በዓላት የአንድ ወገን ወይም ቡድን ብቻ ሳይሆኑ የመላው ኢትዮጵያውያን ሆነው የሚገለጡ፤ በተናጥል ተከብረው የሚውሉ ሳይሆን ኢትዮጵያውያን ጎሳና ሃይማኖት ሳይለያቸው በጋራ በአደባባይም በቤትም የሚያከብሯቸው ስለመሆኑ ሕያው ማረጋገጫ ነው፡፡ ከዚህ ባለፈም፣ በዓላቱን ለተለያዩ የፖለቲካዊ አጀንዳ እና የእኩይ ዓላማ ማሳለጫ የሚሆን የሰላም እክልን ለማከናወኛ አድርገው ሲመኟቸው የነበሩ የጥፋት ኃይሎች ሴራ ሳይሳካ በሰላም ተከብረውና ደምቀው ማለፉቸውም፤ ኢትዮጵያውያን በዓላቶቻቸውን ለሰላምና አብሮነት እንጂ ለፀብና ሁከት ያበጁቸው አለመሆኑን ያረጋገጡበትም ነው፡፡

የአዲስ ዘመን መሻገሪያ፣ የጨለማው ዘመን ማብቂያ፣ የብርሃን ብስራት መታያ፣ የአብሮነትና ሰላም ማማ የሆነው የኢሬቻ በዓል ቅዳሜ በሆራ ፊንፊኔ፣ እሑድ ደግሞ በሆራ ሃርሰዴ የሚከበር ይሆናል፡፡ ይሄ በዓል ምንም እንኳን የሰላም አስተምህሮቱ፣ የአንድነት እሴቱ ከፍ ብሎ የሚገለጥ ቢሆንም፤ አሸባሪው ትህነግ ይሄንን እሴት በሚሸረሽር መልኩ የእኩይ ሴራቸው መጠቀሚያ ለማድረግ በሰሩት ስራ ከዓመታት በፊት በዓሉን ለማክበር ከአራቱም የኢትዮጵያ ክፍሎች የተገኙ ንጹሃን ላይ የተፈጸመው ግፍ የሚዘነጋ አይደለም፡፡

ይሄ ደግሞ ዛሬም ድረስ በዜጎች ልብ ውስጥ የማይሽር ጠባሳን ጥሎ ያለፈ፤ ሊደገም የማይገባው የከፉዎች ከፉ ተግባር መሆኑ በሁሉም ዜጎች ዘንድ ቁጭትን የፈጠረ ሆኗል፡፡ ከዛ በኋላ ያሉትም በዓላት ሰላማዊና ወንድማማችነትን ከፍ አድርገው የገለጹ መሆናቸውም ለዚሁ ነው፡፡

የዘንድሮው የመስቀልና ኢሬቻ በዓል የሚከበረውም ኢትዮጵያ በብዙ መልኩ የተቃጡባትን ጥቃቶች እየመከተች ከመሆኑ ጋር ተያይዞ፤ በዓላቱ እሴታቸውን በሚገልጽና ሰላማዊ በሆነ መልኩ መከበራቸው የሚኖረው ፋይዳና መልዕክት ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ ሰሞኑን በሰላምና አብሮነት እንደተከበሩት በዓላት ሁሉ፤ ኢሬቻንም የሰላም፣ የአብሮነትና የባህል እሴት መሰረትነቱን በሚያረጋግጥ መልኩ እንዲከበር ማስቻል፤ እንዲሁም እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም በዓላቶች የሰላም፣ የባህልና አብሮነት መሰረትነት ከፍ ብሎ እንዲገለጥ ማድረግ የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ሊሆን ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


## “ለኢትዮጵያ መንግሥት ስለ ሰላም ማስተማር ማለት ለዓሣ ዋናን ለወፍ መብረርን ማስተማር ነው”

- ዶክተር ዐቢይ አሕመድ
የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር

## የመስቀል በዓልን ምክንያት በማድረግ ትናንት ያስተላለፉት መልዕክት ሙሉቃል

**እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ አደረሳችሁ!**

አስቸጋሪው የክረምት ወቅት ወጥቶ፣ የጠራውና አስደሳቹ የመጸው ወቅት በሚጀምርበት ወቅት ላይ እንገኛለን። የሞላው ወንዝ ይጎድላል፤ ፈታኙ ጭቃ ይደርቃል፤ ጥሻው ይገለጣል፤ ጨለማውም ይበራል፤ ብርዱ ይቀልላል፤ ሜዳና ተራራው በአበባ ያጌጣል። በዚህ ወቅት ነው ተሠውሮ የኖረው መስቀል የተገኘበትን በዓል የምናከብረው።

ኢትዮጵያውያን የሚያስተሳስረን ገመድ ሊበጠስ የማይችል ጠንካራ መሆኑን ከሚያሳዩን ወቅቶች አንዱ ወርሃ መስከረም ነው። አብዛኞቹ የሀገራችን ብሔረሰቦች የዘመን መለወጫ በዓላቸውን፣ ወይም ደግሞ የዓመቱን ታላቅ የምስጋና በዓላቸውን የሚያከብሩት በዚህ በመስከረም ወቅት በተቀራራቢ ጊዜ ነው። ይህ እንደ እንግዳ ደራሽ፣ እንደ ውሃ ፈሳሽ በድንገት ወይም በአጋጣሚ የሆነ አይመስልም። መነሻው አንዳች የጋራ ዕሳቤ እንደሚኖረው ይጠቁመናል። መነሻው የአንድነታችን፤ የአከባበሩ ልዩ ልዩ መሆን ደግሞ የኅብራዊነታችን ማሳያ ነው።

በአብዛኛው አከባበራችን ደመራው፣ ችቦው፣ የወጣትና የልጆች ፌሽታ፣ ለሽማግሌዎች የሚሰጠው ቦታ፣ ምርቃቱ፣ መልካም ምኞቱ ተቀራራቢ ነው። ይህ ነገር ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ ተመሳስሎና ተቀራርቦ ሲከበር ስናይ፣ ኢትዮጵያ የምትባለው ሀገራችን የተሣሠረችበትን ውስጣዊ ሥር እንድንመረምር ያደርገናል።

ደመራው ሲለኮስ ጨለማው በብርሃን፤ ቁርና ብርዱ በሙቀት፤ ድብርቱ በተስፋ ይተካል። አስቸጋሪውንና ፈታኙን ወቅት መሻገራችንን ደመራው ያበሥራል። ማንም ባይነግረንም የመስኩ አበባና የሰማዩ ጥራት፣ የወፎች ዝማሬና የጅራፉ ጩኸት መስከረም እንደጠባ ይመሰክራል። አበባው ወደ ፍሬ፣ ፍሬው ወደ ምርት የሚሸጋገረው በዚህ ወቅት ነው። በጎመን የከረመ ማጀት በገብስ ገንፎና በልዩ ልዩ እሸት ሰብሎች መሞላት ይጀምራል። ከክረምቱ ጋር አስፈሪ የነበሩት ወንዞች በመስከረሙ ግርማ ጉልበታቸው ላልቶ ዘመዳሞች ለመጠያየቅ፤ ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታቸው ለመመለስ ይሰናዳሉ። ወቅቱ ይዟቸው በሚመጣቸው ክብረ በዓላትና ልዩ ልዩ ሁኔታዎች ምክንያት መስከረም ለኢትዮጵያችን ትልቅ ተምሳሌት ነው።

ውድ ኢትዮጵያውያን፣

በአስቸጋሪና በፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ አልፈን እዚህ ደርሰናል። መንገዳችን ጨለማ፣ እግራችን ቄጤማ እንዲሆን ብዙ ተሠርቶብናል። ከድጡ ወደ ማጡ እንድንወርድ ያልተፈተለ ሤራ የለም። እንጀራችንን የበሉ ተረከዛቸውን አንስተውብናል። ወንዙ እንዲሞላብን፣ ጎርፉ እንዲደርስብን፣ ናዳ እንዲወርድብን ብዙ ተሠርቶ ነበር። የኢትዮጵያ አምላክ ግን አሳልፎ አልሰጠንም።

ስለ ረሃብ እየተነገረብን፣ ምድሪቱ አትረፍርፋ ሰጠችን። ስለ በረሃማነት እየተሟረተብን ሀገራችን አረንጓዴ ለበሰች። ስለ ኪሣራ እየተለፈለፈ፣ ኢኮኖሚያችን ፈተናዎቹን እየተሻገረ ቀጠለ። ከግራ ከቀኝ እየተዋከብን ሦስተኛውን ዙር የሕዳሴ ግድብ ሞልተን ተርባይናችንን አስነሣን። እንድንለያይ መዓት እየተወራ፣ የሕዝባችን አንድነት እንደ ብረት ጠነከረ፤ እንደ አልማዝ አበራ። ደከመዋል ተብሎ ሲዘመትብን፣ በጽናት ቆመን አሳየን። የትም አያደርሷቸውም የተባልንባቸው ፕሮጀክቶቻችን በመጠናቀቅ ላይ ናቸው።

ይህ ሁሉ አልሳካ ሲል ደግሞ ትእግስታችን እንደ ፍርሃት፣ ሰላም ፈላጊነታችን እንደ ድክመት ተቆጥሮ ሦስተኛ ዙር ጥቃት ተፈጸመብን። የታገስነው በዚህም ሆነ በዚያ ወገን የሚያልቀው የእኛው ሕዝብ ነው ብለን ነው። እነሱ ሲከፉ እኛ የለዘብነው፣ የአንድ ሀገር መንግሥትና የአንድ ሀገር አመጸኛ እኩል ለሕዝብ አያስቡም ብለን ነው። ከጸብ ይልቅ ፍቅር ይሻላል ስንል ምላሹ እብሪት እየሆነብን ጭምር በንግግር ፋንታ ኃይል የመጠቀም ፍላጎት አላደረብንም። ከጦርነት በላይ ከሰላም እናተርፋለን ብለን እየተወጋንም ቢሆን የሰላም እጃችን ከመዘርጋት አልተቆጠብንም። ሰላም ግን በአንድ ወገን ፍላጎት ብቻ አይመጣም።

በዚህ የተነሣ ሀገራዊ ሕልውናችንን ለማስጠበቅ ስንል ወደ መከላከል እንድንገባ ተገድደናል። የዛሬው ብቻ ሳይሆን የመጭውም ትውልድ አደራ አለብን። ኢትዮጵያን ከመጥፋት ለመታደግ፣ ሕዝብን ከብተና ለማዳን እና ሀገር እንደ ሀገር ቀጥላ የልጅ ልጆቻችን ሉአላዊነት ኢትዮጵያን እንዲወርሱ ስንል የመጨረሻውን የመከላከል አማራጭ ወስደናል። አሁንም እያደረግን ያለነው የመከላከል ውጊያ ይኼንን ታሪካዊ አደራ ለመወጣትና ብሔራዊ ጥቅሞቻችንን ከአደጋ ለመከላከል ያሰበ ነው።

ለኢትዮጵያ መንግሥት ስለ ሰላም ማስተማር ማለት ለዓሣ ዋናን ለወፍ መብረርን ማስተማር ነው። ‹ሰላም› ራሷ የኢትዮጵያ መንግሥት የከፈለላትን ዋጋ ያህል የከፈለላት የለም። የገጠመን ወረራ በሰላማዊ መንገድ እንዲጠናቀቅ ከሚፈለግብን በላይ አድርገናል። የእኛን ጥረት በተገቢ መንገድ የሚያወድስና የሌላኛው ወገን እምቢታ በተገቢው ልክ የሚያወግዝ ግን ጥቂት ነው። ለሰላም የተዘረጉ እጆች ሰላምን የሚመርጡት፣ ጦር ለመያዝ ስለማይችሉ አይደለም፤ ሰላምን ስለሚመርጡ ብቻ ነው። ለሰላም የዘረጋነው እጅ ምንም ዋጋ ስላላገኘ ጦር እንዲይዝ እየተገደደ ነው።

በተለያዩ አካባቢዎች፣ በከተማና በገጠር፣ በአርሶና በአርብቶ አደር መንደሮች፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር፣ በመሐልና በግንባር ሆናችሁ የብርሃነ መስቀሉን በዓል ለምታከብሩ ሁሉ፤ አንድ ነገር ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ። ኢትዮጵያ በዚህ ዓመት በሁለት እጆቿ እየሠራች ፈተናዋን ትሻገረዋለች። በአንድ እጇ ብሔራዊ ጥቅሟን በሚገባ አስጠብቃ ችግሯን ለመጨረሻ ጊዜ ለመፍታት ትታገላለች። በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝባችን በወዙ ጎተራው እንዲሞላ፤ ምሳውን በብድር ሳይሆን ከራሱ ማሳ ዘግኖ እንዲመገብ የሚችልበትን ስትራቴጂ ነድፈን መንቀሳቀስ እንጀምራለን።

ይህ ጉዞአችን “የሌማት ትሩፋት” ይባላል። ዓላማው በቀላል መንገድ ገበታችንን በተመጣጠነ ምግብ መሙላት ነው። የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ፣ ቀላል የዶሮ ርባታ፣ ቀላል የወተት ላሞች ርባታና የዓሣ ርባታን ይይዛል። አሁን ያለንበት ዘመን በአነስተኛ ቦታዎች፣ ቀላል ቴክሎጂዎችን በመጠቀም፣ በምግብ ራሳችን ለመቻል የሚያስችሉ ዕድሎች የተፈጠሩበት ዘመን ነው። ታላላቅ የእርሻ መሬት የሌላቸው ሀገሮች ይሄን መንገድ ውጤታማ ሆነውበታል። አረንጓዴ አሻራን ውጤታማ እንዳደረግነው ሁሉ፣ ወገባችንን አሥረንና እጅጌያችንን ሰብስበን ጎተራና ማጀታችን እንዲሟላ ከዚህ ዓመት ጀምሮ ታጥቀን እንሠራለን።

የመስቀል በዓል ያለፈውን ፈተና የምናስወግድበትና ለመጪው ተስፋ የምንሰንቅበት ነው። የአከባበሩ ሥነ ሥርዓትና የሽማግሌዎች ምርቃት ይሄንን ያሳየናል። ኢትዮጵያም በዚህ ዓመት የከረሙ ችግሮቿን እንድትፈታና ገበታዋን ለልጆቿ በሚያስፈልጋቸው ምግብ እንድትሞላ፣ ኢትዮጵያን የምንወድ ሁሉ ቆርጠን እንድንነሳ በዚህ አጋጣሚ ጥሪ አቀርባለሁ።

በድጋሚ እንኳን ለመስቀል በዓል አደረሳችሁ፣ አደረሰን።

ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!!

**ፈጣሪ ኢትዮጵያና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

**መስከረም 16/2015 ዓ.ም**

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

በ(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

# "ምሥጢረ በዓላት"

የመንደርደሪያችን ማዋዣ፤
"ክረምት አልፎ በጋ፤ መስከረም ሲጠባ፣
አሮጌው ዓመት አልፎ፤ አዲሱ ሲተካ፣
በአበቦች መዓዛ፤ እረክቷል ልባችሁ፣
ሕዝቦች ሁሉ በጣም እንኳን ደስ አላችሁ::"

እነዚህ ስንኞች በዜማ ተለውሰው የተንቆረቆሩት ከግማሽ ክፍለ ዘመን በፊት በተወዳጁ ድምጻዊ በጥላሁን ገሠሠ አማካይነት ነበር:: ዜማና ግጥሙ ባለፉት ዘመናት ብቻም ሳይሆን ለሚቀጥሉት ረጂም ዓመታትም ሳይደበዝዙና ትርጉማቸው "ሳይወይብ" ከትውልድ ትውልድ እንደሚሸጋገሩ ተስፋ እናደርጋለን:: እንዴት ቢባል "የጥበብ ዕድሜ ከሰው ዕድሜ የላቀ ስለሆነ" - የሚለው መልስ ይሆናል::

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ሕዝበ አዳም በነቂስ ተዘጋጅቶና አደባባይ ወጥቶ፣ ቤቱን አድምቆና አስውቦ፣ወዳጅ ዘመዶቹን ሰብስቦና ጋብዞ የሚያከብራቸውንና ፌሽታ የሚያደርግባቸውን ታላላቅ በዓለት አስመልክቶ የሚወጡት የምሁራን ምርምሮችና የጥናት ውጤቶች የዘርፉን በሳሎች ብቻ ሳይሆን በርካታ የዓለማችንን ዜጎች ሳይቀር "አሃ! ይሄም አለ እንዴ?" እያሰኙ ማስገረማቸው አልቀረም::

ይህ ጸሐፊ ዋነኛው የሥልጠናው መስኩ በድንበር ዘለል ተግባቦት (Intercultural Communicatione) ላይ ስለሆነ በየጊዜው የሚወጡትን ጥናቶች የሚከታተለውና የሚማረው ልብ ተቀልብ ሆኖ ነው:: የአዳዲስ ግኝቶቹ ይዘት ወደ ኋላ ግድም ስለሚብራራ በዓላትን አስመልክቶ በአንዳንድ የሀገራችን ምሁራንና "በእናውቃለን ባይ ጥራዝ ነጠቆች" አማካይነት የሚሰጡትን አስተያየቶች "ገረፍ" አድርገን እናልፋለን::

"እንኳን ለአዲሱ ዓመት በሰላም አደረሰህ/አደረሰሽ!" ሲባሉ "ዓመቱን ማን አዲስ አደረገው? ምንም አዲስ ነገር የለውም:: ወራቱ ዞረው የሚመጡት ያው የትናንቶቹ መስከረም፣ ጥቅምት፣ ህዳር ናቸው:: ቀናቱም ከሰኞና ከማክሰኞ ዘወትራዊ ዕለታት የተለዩ አይደሉም:: የዓመቱ ክፍለ ወራት መፀው፣ ፀደይ፣ በጋና ክረምቱም እነዚያው የምናውቃቸው ናቸው:: ከሰማይ በታች ምንም አዲስ ነገር የለም::" እያሉ በጎልዳፋ አመለካከት፤ "እንቃሪ አስተያየት" የሚሰጡ በርካታ ሰዎች ሳያጋጥሙን አልቀሩም::

አንዳንዶች "በቡሃ ላይ ቆረቆርን" እየተረቱ "እንኳንስ በዓላትን ለማክበር ቀርቶ ድህነታችን ራሱ እያናወዘ መኖር አስጠልቶናል ወዘተ." በማለት ከመደበኛ ሥራ የመገለሉን ምክንያትና ለበዓል የሚወጣውን ወጭ እያሰሉ አጥብቀው ሲያማርሩና ሲተቹ መስማት አንግዳችን አይደለም:: ምክንያቶቻቸው ሁለቱ ብቻ ሳይሆኑ በርከት ሊሉ እንደሚችሉ እንገምታለን:: እውነት ሀሰቱን ለጊዜው ትተን፤ እነርሱ ሰበብ እየደረደሩ ከበዓላት አከባበር ጋር ጠብ የፈጠሩ ይምሰሉ እንጂ የትኞቹም የዓለማችን ሕዝቦችና ሀገራት "የእኔ ብቻ" የሚሉትና ከሌሎች የሰው ዘሮች ጋር የሚጋሯቸው በርካታ በዓላት እንዳሉ ይታወቃል::

ለአጠቃላይ ግንዛቤ እንዲረዳን በዓላትን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች አቧድኖ መመልከት ይቻላል:: በመጀመሪያው ክፍል የሚመደቡት ሃይማኖታዊ (መንፈሳዊ) እና ባህላዊ የምንላቸው በዓላት ናቸው:: በዚህ ዘርፍ የተለዩት በዓላት አንድም የዓለም ሕዝቦች የጋራ "ይሁንታ" የሰጧቸውና መሠረታቸው በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ የተመሠረቱ ናቸው:: ለምሳሌ፡- በክርስትና እምነት በምዕመናን ዘንድ ከፍ ባለ መንፈሳዊ ክብር (Reverence) የሚከበሩትን የመስቀል፣ የልደተ ክርስቶስ፣ የስቅለትና የትንሣኤ በዓላትን ይመለከታል:: በእስልምና እምነትም የነብዩ መሐመድ ልደትን (መውሊድ)፣ ኢድ አል ፈጥር (ኢድ)፣ ኢድ አል አድሃ (አረፋ)ን የመሳሰሉትን ማስታወስ ይቻላል:: ከአይሁድ እምነት በዓላት መካከልም የፋሲካን፣ የበዓለ ሃምሳንና የዳስ በዓላት በመባል የሚታወቁትን ለማሳያነት መጥቀስ ይቻላል::

ከባህላዊ እምነቶች መካከልም በዚህ ሰሞን ጎላና ደመቅ ብለው በየብሔረሰቡ እየተከበሩ ያሉትን የዘመን መለወጫና በተለያዩ መንፈሳዊ ምክያቶች ሳቢያ በታላቅ ድምቀትና ፌሽታ የሚዘከሩትን በዓላት ማስታወስ ይቻላል:: የጋሞዎቹ "ዮ! ማስቃላ"፣ የወላይታ ብሔረሰብ "ግፋታ"፣ የሲዳማው "ፍቼ ጨምበላላ"፣ የኦሮሞ ብሔረሰብን የ"ኢሬቻ" በዓላትን በምሳሌነት መጠቆም ይቻላል::

በሁለተኛው ክፍል የሚመደቡት በዓላት የሃይማኖት፣ የብሔርም ሆነ የቋንቋ ገደብ ሳይጫናቸው በመንግሥታዊ ወይንም በፖለቲካዊ ውሳኔ "የእኛ የጋራ በዓል" ተብለው በመሰየም "በብዙኃን ዜጎች ዘንድ በዓለም አቀፍ ወይንም በሀገር ደረጃ የሚከበሩ" የአንድን ሕዝብ ወይንም ቡድን ገናናነትና አሸናፊነትን የሚዘክሩ በዓላት ናቸው:: ለምሳሌ ዓለም አቀፍ የላባደሮች ቀን፣ ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ወዘተ. እና በየሀገሩ የሚከበሩት ከቅኝ ገዢዎች ነፃ የወጡባቸው ቀናትና የድል በዓላት ለምሳሌነት ቅርብ ሊሆኑ ይችላሉ::

በእኛ ሀገርም በካሌንደር ተዘግተው መድፍ እየተተኮሰላቸው የሚከበሩትን እንደ የአድዋና የሚያዝያ 27 ቀን የድል በዓላት፣ ወይንም በሀዘንና በትካዜ የሚከበረውን የየካቲት 12 የሰማዕታት መታሰቢያ ቀንንና ከካሌንደርም ሆነ ከሕዝብ አእምሮ ጭርሱኑ ተፍቆ ሊጠፋ አንድ ኅሙስ የቀረውን አስቀያሚውን የግንቦት ሃያ በዓላት ማስታወስ ለግልጽነት ያግዛል:: ቅድመ ደርግ ዓመታት በታላቅ ክብርና ሞገስ ይከበሩ የነበሩትን የንጉሡን የልደትና የንግሥና ዕለት መታሰቢያ በዓላትንም ወደ ኋላኛው ዘመን አፈግፍጎ ማስታወስ ይቻላል::

የበዓላቱ "የምሥጢር ፍቺ"፤

ቀደም ሲል በሁለት ቡድን ከፍለን በዝርዝር የተመለከትናቸው በዓለት ሲከበሩ በአከባሪዎቹ ሕዝቦች ወይንም በተወሰነው የማሕበረሰብ ክፍልና ቡድኖች የሚፈጠረውን ስሜትና ተጽእኖ በተመለከተ በየጥናቶቹ ተብራርቶ የተገለጸውን እውነታ እንደሚከተለው አሳጥረን እንገልጻለን::

ሃይማኖታዊ ወይንም "መንፈሳዊ" በዓላትን የሚያከብሩ ሕዝቦችና የማሕበረሰብ ክፍሎች በዓላቱን ለማክበር በዋዜማው ቀናትና በበዓላቱ ዕለታት የሚያደርጉትን ዝግጅትና ሽር ጉድ ወይንም ፌሽታውን የሚያደምቁትና የሚንበሸበሹት በተፍታታ ስሜት፣ ተስፋ በሰነቀ እምነትና በተረጋጋ ቀልብ ሰክው ነው::

ወቅታዊው የድህነታቸው፣ የችግራቸው፣ የእጦታቸውም ሆነ የሀዘናቸው ጉዳት እጅግም እንዳዘቦቱ ቀናት ተጫጭኖ አይደብታቸውም:: እነዚህ በዓላት ሲከበሩ ልግስና፣ አብሮነት፣ መረዳዳትና መደጋገፍ ጎልተው ይስተዋላሉ:: አብሮ መብላቱና መጠጣቱ፣ የወትሮ ዓይነት ስሜት ሳይሆን የሚፈጥረው ሰንባች ትዝታን ነው::

ሕዝብን እዬዬ የሚያሰኘው የኑሮና የኢኮኖሚ ጣጣ፣ ፖለቲካው የሚረጨው ፕሮፓጋንዳና ጫና፣ በሀገር ላይ የደረሱ ለየት ያሉ ወቅት ወለድ ችግሮችና መከራዎች ለጊዜውም ቢሆን በበዓላቱ አከባበር ወቅት ስለሚደበዝዙ በሕዝቡና በማኅበረሰቡ የሚስተዋለው እፎይታ፣ የተረጋጋና የሰከነ ስሜት ነው::

ስለዚህም ይላሉ አጥኚዎቹ፡- ሁካታና ግርግር፣ ጦርና የጦር ወሬ፣ ድህነትና የተፈጥሮ አደጋ ወዘተ. እየናጣት አሳር በልታ አሳሯን ባሸከመችን ዓለማችን ላይ እንደነዚህ ዓይነት ሃይማኖታዊና "መንፈሳዊ" ዓላማና ተልእኮ ያላቸው በዓላት መከበራቸው ፋይዳቸው ከፍ ያለ ብቻ ሳይሆን የሰብዓዊነት ክብርም ደመቅ ብሎ የሚገለጽበትና መንፈሳዊ ስክነትና መነቃቃት የሚስተዋልበት ጭምር ነው:: እነዚህን በዓላት ማክበሩ ሊበረታታ እንጂ "ለቁሳዊ ጉዳዮች ብቻ ትኩረት ሰጥቶና የኢኮኖሚ ‹ብክነትን› እንደ ምክንያት እያጎሉ የበዓላቱ አከባበር እንዳይኮነን ምሁራኑ ማጠቃለያቸው ላይ አስፍረዋል::

በአንጻሩም፡- በመንግሥታዊ ትዕዛዝና አዋጅም ይሁን በፖለቲካ ትግል አሸናፊነት ወይንም የድል አድራጊነትንና የአሸናፊነትን ታሪኮች ለመዘከርና ለማስታወስ ታስበው የሚከበሩት ሕዝባዊ በዓላት ልክ እንደ ሃይማኖታዊያኑና ባህላዊ በዓላት ስሜትን ከማረጋጋት ይልቅ ቂምን፣ ያለፈ በደልን፣ መጠቃትን፣ በግፍ መወረርንና መደፈርን አጉልተው ስለሚዘክሩ አከባበራቸው የቀዘቀዘ፣ ስሜትን ከማስከን ጋር ያላቸው ቁርኝትም እጅግም ስለሆነ የሚወደስና የሚናፈቅ አይደለም::

በጥናቶቹ እንደተረጋገጠው ለምሳሌ፡- የዓለም አቀፍ የላብ አደሮች (ሜዴይ)፣ ወይንም የሴቶች በዓል (ማርች ስምንት) የመሳሰሉት በዓላት ሲዘከሩ አክባሪው ማኅበረሰብ ቁጣውን፣ መጠቃቱን ወይንም ግፉን የሚገልጽበት ስሜት እየተብከነከነና በሞቅታ ስሜት እንጂ እንደ ሃይማኖታዊና "መንፈሳዊ" በዓላት ተረጋግቶና ሰክኖ የሚያከብራቸው አይደሉም::

እኛም ብንሆን የድል በዓላቶቻችንን ስናከብር ወራሪዎቹን እየኮነንና ያደረሱብንን የግፍ ወረራ እያስታወስን ስሜታችንን በማስቆጣት እንጂ በተረጋጋና በሰከነ ስሜት እንዳልሆነ የምንረዳው ይመስለናል:: በጥሩ ማሳያነቱ የሚገለጸው ቀደም ሲል የጠቀስነው አይረቤው የግንቦት 20 "በዓል" ነው:: ይህ ዕለት የሚከበረው ጥቂት የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች ቁጤማ ጎዝጉዘውና "ዋንጫ ኖር!" እያሉ በፈንጠዝያ ያከብሩት ካልሆነ በስተቀር ብዙ ዜጎች ዕለቱን የሚያስታውሱት ሀዘናቸውን እየገለጹ፣ መከራቸውን እየዘከሩና የሥርዓቱን ጨቋኝነት አፍ ለአፍ እየተቀባበሉና በተጎዳ ስሜት እየተከዙ ጭምር ነው::

በተለይም ለእንደኛ ዓይነቱ የዕለት ተዕለት ሕይወታችን "ለአፍ ማበሻ ዳቦ ሳይቀር ብርቅ ለሆነብን" ኢኮኖሚው ለሚያንገላታን ዜጎች፣ በፖለቲካው ምክንያት ናላችን እየዞረ መረጋጋት ለራቀንና የጦርነት ዜና ጆሯችንን ጭው አድርጎ ድብርት ውስጥ ለከተተን ሕዝቦች ሃይማኖታዊና ባህላዊ በዓላቶቻችን ስሜታችንን ለጊዜውም ቢሆን ለመፈወስ ትልቅ አቅም እንዳላቸው የምንረዳ ይመስለናል::

ማሕበራዊ ሕይወታችንን ለማነቃቃትና ጫናው በጠነከረበት መንፈሳችን ላይም ሰላምን ለማርበብ ድርሻቸው በቀላሉ የሚታይ አይደለም:: ስለዚህም እነዚህን መሰል በዓላቶቻችንን እየተጋገዝን፣ እየተረዳዳንና እየተደጋገፍን ማክበሩ መልካም ነው:: ይሄም ሲባል ግን በትንሽ በትልቁ፣ በውስን ቡድኖችና አካባቢዎች የበዓላት ቁጥርን በሰበብ አስባቡ እያበራከቱ ከእርሻ፣ ከምርት ተግባራትና ከተግባር ውሎ መዘናጋቱ ይወገዝ ካልሆነ በስተቀር ሊበረታታ አይገባም::

በተመቻቸ ኑሮና ሕይወት ወይንም እጅግም ችግር ባልተጫነው ሁኔታ ውስጥ በመሆን በዓላትን በፌሽታና በደስታ ለማክበር ዕድልና ጊዜ ፊቷን ያላጠቆረችብን ዜጎች ለሌሎች ወገኖቻችን የደስታ ምንጭ መሆንን ፈጣሪም ሆነ ሰብዓዊነታችን ግድ ይለናል:: በተለይም እኩይ የሚለው ቃል ከሚገልጣቸው በላይ "ልጆቻችን" በሚሏቸው ወበከንቱዎች መከራ የወደቀባቸውን የትግራይ ወገኖቻችንን፣ ጦርነቱ የሚያመረቅዝ ደዌ የሆነባቸውን የአፋርና የአማራና አካባቢ ሕዝቦችን፣ የውዶቻቸው ነፍስ በወራሪዎች የተነጠቁ መከረኞችን፣ ከመኖሪያ ቀዬአቸው "በደም ሱሰኞች" የተፈናቀሉትንና የሀዘን ወስከንባይ የተደፋባቸውን ዜጎቻችንን ቅድሚያ ሰጥተን ልናስባቸው ውዴታችን ብቻ ሳይሆን ግዴታችንም ጭምር ነው::

ቤት ንብረታቸው ወድሞ አውላላ ሜዳ ላይ የወደቁትንና የሀገርን ሉዓላዊነት ለማስከበር ላብና ደማቸውን እየገበሩልን ላሉት ጀግኖቻችንና ቤተሰቦቻቸው የደስታና የመጽናናት ምክንያት ሆነን ከስሜት እረፍታችን፣ ከገበታችን ማእድ ልናጋራቸውና ለተወሰኑ ጊዜያችም ሆነ በዘላቂነት ካሉበት ስሜት ወጥተው "እፎይ" እንዲሉ ልናግዛቸውና አለንላችሁ ልንላቸው ይገባል:: ሰላም ይሁን::

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን የማድረጊያ ግብዓት የሆነው ብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ

አንተነህ ቸሬ

መንግሥት የተማከለና በቴክኖሎጂ የታገዘ ብሔራዊ የመታወቂያ ስርዓት እንዲኖር እንቅስቃሴ የጀመረው ከ10 ዓመታት በፊት ነበር፡፡ በወቅቱ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት እና የመረጃ መረብ ደኅንነት ኤጀንሲ ከሌሎች ተቋማት ጋር በመቀናጀት አንዳንድ እንቅስቃሴዎችን የጀመሩ ቢሆንም፣ ስራዎቹ በብዙ መሰናክሎች ምክንያት የሚፈለገውን ተጨባጭ ውጤት ሳያስገኙ ቀርተዋል፡፡

በለውጡ ማግስት የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ስርዓትን እውን የማድረጉ ኃላፊነት በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የተሰጣቸው የሰላም ሚኒስቴር እና የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፤ በትብብር ያከናወኗቸው የቅድመ-ዝግጅት እንዲሁም የቴክኒካዊና ሕጋዊ ማዕቀፎች ተግባራት የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት ትግበራው መስመር እንዲይዝ ማስቻላቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከእነዚህ ተግባራት መካከል የብሔራዊ መታወቂያ ስርዓቱን ጽንሰ ሃሳቦችን ያብራሩና አቅጣጫ የጠቆሙ የስትራቴጂያዊና ሕጋዊ ሰነዶች ዝግጅት እንዲሁም የሙከራ ትግበራዎች ተጠቃሽ ነው፡፡

ካለፈው ዓመት ጀምሮ ተጠሪነቱን ለጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ያደረገው የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ፕሮጀክት፤ የ‹‹ዲጂታል ኢትዮጵያ›› እቅድ እውን ይሆናል ተብሎ እስከታቀደበት እስከ 2018 ዓ.ም (Digital Ethiopia 2025) ድረስ 95 በመቶ ለሚሆነው የሀገሪቱ ጎልማሳ ሕዝብ የዲጂታል መታወቂያ ለመስጠት እቅድ ይዞ እየሰራ ነው፡፡ የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ፕሮጀክት የቅድመ ትግበራ ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቶ ወደ ብሔራዊ ትግበራ መግባቱን ሰሞኑን ‹‹ዓለም አቀፍ የመታወቂያ ቀን›› (International Identity Day) ሲከበር ይፋ አድርጓል፡፡

የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ፕሮግራም ዋና ዳይሬክተር አቶ ዮዳሄ አርዓያሥላሴ መታወቂያ ማግኘት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዘላቂ የልማት ግቦች (UN Sustainable Development Goals) ውስጥ ከተካተቱ ጉዳዮች መካከል አንዱ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት፤ መንግሥት አንድ የተማከለ የመታወቂያ ስርዓት ለመዘርጋት አቅዶ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ከ10 ዓመታት የበለጠ ጊዜ ያስቆጠረው ይህ ሃሳብ፤ ቀደም ሲል የነበረው ዕይታ ደህንነት ተኮር የነበረ ሲሆን፣ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ደግሞ የመታወቂያ ስርዓት እሳቤውን አገልግሎት ተኮርም ለማድረግ እንቅስቃሴ ሲደረግ ቆይቷል፡፡

በ2012 ዓ.ም የመጀመሪያው የላቦራቶሪ ሙከራ ትግበራ ይፋ የተደረገ ሲሆን፣ ከ2013 ጀምሮ ደግሞ ስራው በመስክ ትግበራ ደረጃ ይፋ ተደርጓል፡፡ እስከ አሁንም አንድ ሚሊዮን ሰዎች ለዲጂታል መታወቂያው ተመዝግበዋል፡፡ ‹‹ዲጂታል ኢትዮጵያ››ን እውን ለማድረግ እስከታለመበት እስከ 2018 ዓ.ም (Digital Ethiopia 2025) ድረስ 70 ሚሊዮን ዜጎችን በዲጂታል መታወቂያ በመመዝገብ አስተማማኝ የመታወቂያ ስርዓት ለመገንባት እቅድ መያዙንም ጠቁመዋል፡፡

‹‹ዲጂታል መታወቂያ ‹‹አንተ ማን ነህ/ማን ነሽ?›› የሚለውን ጥያቄ መመለስ የሚችል ስርዓት (Proof of Identity) ነው፡፡ በቅርቡ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደሚጸድቅ የሚጠበቀውና የብሔራዊ ዲጂታል የመታወቂያ ስርዓት ሕጋዊ መሰረት እንዲኖረው የሚያደርገው የዲጂታል መታወቂያ ረቂቅ አዋጅም የተቀረፀው በዚህ እሳቤ ነው፡፡ የዲጂታል መታወቂያ ምዝገባ አስገዳጅ ያልሆነና በነፃ ፍላጎት ላይ ተመስርቶ የሚከናወን ነው፡፡

ምዝገባው በአዋጁ አስገዳጅ ያልተደረገ ቢሆንም፣ አዋጁ ግን ለተቆጣጣሪ ተቋማት የማስገደድ መብት ይሰጣል፡፡ ተቋማቱ ‹‹ይህ መታወቂያ ለዚህ ዘርፍ አስገዳጅ ነው›› ብለው እንዲወስኑ የማስገደድ መብት ይሰጣቸዋል፡፡ መንግሥት (የሚመለከተው የመንግሥት አካል) መታወቂያ ለሚፈልግ ዜጋ መታወቂያ የማቅረብ ኃላፊነት እንዳለበትም በአዋጁ ላይ ተጠቅሷል፡፡ የዲጂታል መታወቂያ አገልግሎት ሁሉንም ዜጋ የሚመለከት ፕሮጀክት በመሆኑ በማንኛውም የእድሜ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሁሉም ዜጋ ለዲጂታል መታወቂያ

**ኢትዮጵያ ከመታወቂያ ጋር ተያያዥ የሆኑ ችግሮች ከሚስተዋልባቸው ሀገራት መካከል አንዷ ናት፡፡ የመታወቂያ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን መብትን ለመጠየቅና ግዴታን ለመወጣት የሚያስችል ግብዓት ነው፡፡ ከመታወቂያ ጋር ተያያዥ የሆኑ ችግሮችን ለመፍታት ዘመናዊ የመታወቂያ ስርዓትን መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡**

መመዝገብ ይችላል፡፡ ምዝገባው በነፃ የሚከናወን ሲሆን ሌሎች የፕሮጀክቱ ደረጃዎችና ተግባራት ግን ክፍያ የሚጠየቅባቸው ይሆናሉ›› ይላሉ፡፡ ከምዝገባና ማረጋገጫ ማግኘት በኋላ ያለው በመታወቂያው አገልግሎት የማግኘት ተግባር (‹‹መታወቂውን ከያዝኩ በኋላ ምን አገኝበታለሁ?›› ብሎ መረዳት) እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አቶ ዮዳሄ ይናገራሉ፡፡

ዜጎች ለዲጂታል መታወቂያ ሲመዘገቡ የሚሰበሰቡት መረጃዎች ተገቢነት ከመታወቂያ ስርዓቱ አስተማማኝነት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንደሚኖራቸው ይታወቃል፡፡ በዚህ ረገድ ዜጎች ለዲጂታል መታወቂያ ሲመዘገቡ የሚሰበሰቡት መረጃዎች ጥንቃቄን በተላበሰ የዓለም አቀፍ ጥናት የታገዘ እንዲሁም በኢትዮጵያ ያሉ አሰራሮችን ከግምት ውስጥ ባስገባ አካሄድ የሚሰበሰቡ እንደሆኑ አቶ ዮዳሄ ያስረዳሉ፡፡ ‹‹ስም፣ ፆታ፣ አድራሻና የትውልድ ዘመን አስገዳጅ መረጃዎች (Mandatory Attributes) ናቸው፡፡ ይህም የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ አሰራሩ፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ‹‹ሕጋዊ ማንነት››ን (Legal Identity) ከሚያብራራበት ትርጓሜ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ያደርገዋል›› ይላሉ፡፡

በ2015 ዓ.ም 12 ሚሊዮን ዜጎችን ለመመዝገብ የተያዘውን እቅድ ለማሳካት በራስ የቴክኖሎጂ አቅም ላይ በመመስረት የምዝገባ ስርዓቱ በመንግሥት ኔትወርክ በወረዳና በቀበሌ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ኤጀንሲ ኔትወርኮች አማካኝነት አገልግሎቱን በስፋት ለማቅረብ እንደሚሰራም ዋና ዳይሬክተሩ ይገልፃሉ፡፡

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ሃላፊ እና የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር አቶ ተፈሪ ፍቅሬ ኢትዮጵያ ከመታወቂያ ጋር ተያያዥ የሆኑ ችግሮች ከሚስተዋልባቸው ሀገራት መካከል አንዷ እንደሆነች ይጠቅሳሉ፡፡ የመታወቂያ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን፣ መብትን ለመጠየቅና ግዴታን ለመወጣት የሚያስችል ግብዓት መሆኑን ጠቁመው፤ ከመታወቂያ ጋር ተያያዥ የሆኑ ችግሮችን ለመፍታት ዘመናዊ የመታወቂያ ስርዓትን መዘርጋት አስፈላጊ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

እርሳቸው እንደሚያብራሩት፤ በቴክኖሎጂ የታገዘ የዲጂታል መታወቂያ አገልግሎት፤ ዜጎች የመታወቅ መብት እንዲያገኙ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መብቶቻቸውን የመጠቀም እድላቸውን እንዲያሰፉ፣ በአገልግሎት ሰጪነትና ተቀባይነት መካከል የሚኖር እምነት እንዲዳብር፣ ምጣኔ ሀብታዊ ሽግግር እንዲኖር፣ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን፣ የሐብት ብክነት እንዲቀንስ፣ አካታችነት እንዲጎለብት፣ ፍትሃዊ ሀብት ክፍፍል እንዲኖር፣ በፖሊሲ ቀረፃና በልማት ስራዎች ትግበራ ላይ ድግግሞሽ እንዳይኖር፣ እንዲሁም ግልጽና የተሳለጠ የአገልግሎት ስርዓት ለመዘርጋት ያስችላል፡፡ አስተማማኝ፣ ተደራሽና የሀገሪቱን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እድገት እና ተገማችነት ለማሳደግ፣ የነዋሪዎችን ሰላምና ደህንነት ለመጠበቅ እንዲሁም አስተዳደራዊና የፍትህ ስርዓቱን ለማጠናከር ያግዛል፡፡

አቶ ተፈሪ በኢትዮጵያ ዘመናዊ የመታወቂያ ስርዓት አለመኖሩ ያስከተላቸውን ችግሮች ሲያብራሩ ‹‹በሀገራችን ዘመናዊ የመታወቂያ ስርዓት ባለመኖሩ ዜጎችን ከሌሎች ግለሰቦች በልዩ ሁኔታ ለመለየት እንዲሁም የዜጎችን ትክክለኛ የዲሞግራፊ መረጃ ለማወቅ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት አልተቻለም፡፡ ይህም በአግባቡ ሊዘጋጁና ሊተገበሩ የሚገባቸው የህዝብ ብዛትና ምጣኔ ሀብታዊ እንዲሁም ወሳኝ የማኅበራዊ ልማት መለኪያዎች አግባብነት ያለውን አሰራር ተከትለው እንዳይሰበሰቡ፣ እንዳይጠናቀሩና እንዳይተነተኑ በማድረግ የዜጎች መረጃ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ቀረጻና ትግበራ የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ለማድረግ እንዲሁም ግብረ መልስ ለመስጠት አስፈላጊ የመረጃ ምንጭ ሆኖ የሚያገለግልበት ምቹ ሁኔታ እንዳይኖር አድርጓል›› ሲሉ ያብራራ፡፡

በሀገሪቱ በስፋት ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የቀበሌ የነዋሪነት መታወቂያ ስርዓት ዜጎች ሕጋዊ ነዋሪ መሆናቸውን ለማረጋገጥና የተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚጠቀሙበት ስርዓት መሆኑን ጠቅሰው፣ ይህ ስርዓት ዜጎች ከሚኖሩበት አካባቢ ዝቅተኛ የአስተዳደር መዋቅር በቀላሉ የሚያገኙት የመታወቂያ አቅም ቢሆንም በርካታ ጉድለቶች አሉበት ይላሉ፡፡ የቀበሌ መታወቂያ በታችኛው የአስተዳደር መዋቅር ብቻ የሚመዘገብና ማዕከላዊ የምዝገባ ቋት የሌለው መሆኑን ጠቅሰው፣ አንድ ሰው ከተለያዩ ቦታዎች በርካታ መታወቂያዎችን እንዲያወጣ እንደሚያስችለውም ነው የተናገሩት፡፡ ጠንካራ መለያዎች የሌሉት በመሆኑም በቀላሉ ሊጭበረበር እንደሚችል ያመለክታሉ፡፡ አንድ ሰው በተለያዩ ስሞችና ማንነት በርካታ መታወቂያዎችን በመያዝ በተለያዩ የወንጀል ድርጊቶች ውስጥ ሲሳተፍ መመልከት የተለመደ መሆኑንም ነው የገለጹት፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚያገለግል ወጥ፣ አስተማማኝና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደራጀ የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት ለመዘርጋት በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ሙከራዎች ሲደረጉ መቆየታቸውን አስታውሰው፣ ውጤታማ ተግባራትን ማከናወን ግን እንዳልተቻለ ይጠቅሳሉ፤ ይህን ችግር ለመፍታት የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት ለመዘርጋት እየተሰራ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

‹‹የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂ ጸድቆ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ ስትራቴጂው ትኩረት ከሰጣቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት ነው፡፡ ዜጎችን የዲጂታል መታወቂያ ባለቤት በማድረግ የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂ እቅዱን ለማሳከት የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ፕሮጀክትን በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ስር በማደራጀትና አስፈላጊውን የሰው ኃይል ግብዓት በማሟላት ወደ ስራ የተገባ ሲሆን፣ ስራው በሕግ ማዕቀፍ የተደገፈ እንዲሆንም የዲጂታል መታወቂያ ረቂቅ አዋጅ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ጸድቆ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተልኳል›› በማለትም አሰራሩን ለመዘርጋት እየተከናወኑ ስላሉ ተግባራት ይናገራሉ፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ተግባራት መንግሥት ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት መስጠቱን የሚያመለክቱ ማሳያዎች እንደሆኑ የተናገሩት አቶ ተፈሪ፤ ባለድርሻ አካላትም የዲጂታል መታወቂያ ስርዓትን ከስራዎቻቸው ጋር እንዲያስተሳስሩና ግንዛቤ እንዲፈጥሩም አሳስበዋል፡፡

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር አቶ ሰለሞን ሶካ በበኩላቸው እንዳሉት፤ የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ለዲጂታል ትራንስፎርሜሽን መሰረት ከሆኑ ግብዓቶች መካከል አንዱ ነው፤ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር አጠቃላይ የዲጂታል አሰራሩ ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን የሚያስችል ስራ ጀምሯል፡፡

የዲጂታል መታወቂያ የዜጎችን የሳይበር ደህንነት ለመጠበቅና አንድ ሰው አንድ ብቻ እንደሆነ ማረጋገጫ ለመስጠት፣ የአገልግሎት መተማመኛ መሰረት ለመዘርጋት፣ የዜጎችንና የአገልግሎት ሰጪዎችን ደህንነት ለመጠበቅ ያስችላል ያሉት አቶ ሰለሞን፣ በተጨማሪም የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂው ዓላማ በመንግሥትም ይሁን በግሉ ዘርፍ የሚቀርቡ አገልግሎቶች ማጭበርበሮችንና የሳይበር ውንጀላዎችን በሚቀርፍ አግባብ ለዜጎች ተደራሽ እንዲሆኑ ማስቻል መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያለውን የንግዱን ማኅበረሰብ በዘመናዊ መታወቂያ ለመለየት የሚደረጉ ጥረቶች በቂ እንዳልሆኑ የተናገሩት የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዝደንት ኢንጂኔር መላኩ እዘዘው፤ የዲጂታል መታወቂያ አሰራር ሲተገበር የብድር፣ የሎጂስቲክስ፣ የግብር አከፋፈል አሰራሮችንና መረጃዎችን ለንግዱ ማኅበረሰብ ቀልጣፋና ግልጽ በሆነ አሰራር ለማቅረብ እንደሚያግዝ እንዲሁም መንግሥት ለሚያዘጋጃቸው እቅዶችም ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት እንደሚያስችለው ተናግረዋል፡፡ ‹‹አገልግሎቶች ግልጽና ቀልጣፋ የሚሆኑት አንድ ሰው አንድ መታወቂያ ብቻ ሲኖረው ነው፡፡ የዲጂታል መታወቂያ ይህን ለማሳካት ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል›› ብለዋል፡፡

በቴክኖሎጂ የተደገፈ ብሔራዊ የዲጂታል መታወቂያ ስርዓት መዘርጋት ከአስር ዓመቱ ሀገራዊ የልማት እቅድ ስትራቴጂካዊ ምሰሶዎች (Strategic Pillars) መካከል አንዱ የሆነውን የቴክኖሎጂ አቅም እና ዲጂታል ኢኮኖሚን ለመገንባት ወሳኝ ግብዓት በመሆኑ ዲጂታል መታወቂያን ለዜጎች በማዳረስ የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ ሀገራዊ እቅድን ማሳካት ይገባል፡፡

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የአንዳንድ ምዕራባውያን መገናኛ ብዙሃን የሀሰት ዘገባዎች አንደምታው

**አስመረት ብስራት**

አንዳንድ የምዕራባውያን መገናኛ ብዙሃን ከሙያዊ ስነምግባር ውጪ የሆኑ ዘገባዎችን ማሰራጨት በተለይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የተለመደ መደበኛ ተግባራቸው ሆኗል። አሁን አሁን ደግሞ ይበልጥ በኢትዮጵያ ላይ ሀሰተኛ እና የተዛቡ ዘገባዎችን በማቅረብ ጭምር የዓለምን ማህበረሰብ በማሳሳት ተግባር ላይ ተጠምደዋል። ሀገሪቱ በሰላም ዙሪያ ያላትን ተነሳሽነትና ዝግጁነት ለዚህም እያደረገች ያለችው ስራ ለመዘገብ ደግሞ ብዕራቸው ይነጥፋል። ያዩና የሰሙትን እንዳላዩ ማለፍ በሌላ በኩል ደግሞ በሬ ወለደ ቅጥፈታቸውን ማራገብ የዘወትር ስራቸው ሆኗል።

ለምሳሌ ያህል በርካታ የእርዳታ እህል ወደ ትግራይ ክልል እየገባ ባለበት ሁኔታ፤ የኢትዮጵያ መንግስት ረሀብን እንደ ጦር መሳሪያ እየተጠቀመ ነው የሚል አንድምታ ያላቸው ዜናዎች ሲያስተላልፉ ነበር ። የእርዳታ እህል የጫኑ የአለም ምግብ ፕሮግራም መኪኖች ደግሞ የእርዳታውን እህል ይዘው ከገቡ በኋላ ህወሓት ለጦርነት መገልገያ ሲያውላቸው፤ ለሰብአዊ አገልገሎት የገባን የህጻናት አልሚ ምግብ ፤መድህኒትና ሌላውን ከታለመለት አላማ ውጪ ሲውል አይቶ እንዳላዩ ከመሆን ያለፈ ዘገባ ሲሰሩ አልታዩም። በዝምታ ከመመልከት ያለፈ ምንም ሲሉ አልተደመጡም። እንዳውም ህወሓት በመሬት ላይ የተሸነፈ ሲመስላቸው የአድኑት፤ የድረሱለት ድምጻቸውን ቃላቀባይ በሚመስል መልኩ የህወሓትን መግለጫዎች ሲያራግቡና ሲያስተጋቡ ይታያሉ።

በተለይ ቢቢሲ አማርኛው፣ አልጀዚራ፣ሮይተርስ፣ሲኤንኤን ፤ አልህራም እና ሌሎችም ጋዜጦች ጭምር በተለይ የተዛባ እና ሀሰተኛ መረጃዎችን በማቅረብና በማውጣት ስራ ላይ ተጠምደው ዛሬ ለደረስንበት ደረጃ ደርሰዋል። በቅርቡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ምክር ቤት የሰብአዊ መብቶች የባለሙያ ቡድን ያቀረበውን «ሪፖርት» የኢትዮጵያ መንግስት እንደማይቀበለው ቢያሳውቅም የመንግስትን አቋም ሳይሆን እነሱ በኢትዮጵያ ላይ ተጽዕኖ ለማሳረፍና የኢትዮጵያን ስም ለማጠልሸት ያስችላል ብለው በሚፈልጉት መንገድ ሲዘግቡት ተስተውለዋል።

ለመሆኑ እነዚህ የምዕራባውያን መገናኛ ብዙሃን በዚህ ሙያዊ ባልሆነና ወደ አንድ ጎን ባደላና በተንሻፈፈ ዘገባ ላይ የተጠመዱት ለምን ይሆን? ከዚህስ ምን ያተርፋሉ ? ስንል የሙያው ባለቤት የሆኑ ምሁራንና ጋዜጠኞችን ጠይቀናል።

የአሀዱ ቲቪና ሬዲዮ ስራ አስኪያጅ ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠ በሰጡት አስተያየት ፤ አሸባሪው ህወሓት የቀደመ ታሪኩ ሀሰተኛ ነገሮችን በመፈብረክ መረጃ ማሰራጨት ነው።ከዛሬ 50 ዓመት በፊት ሲፈጠር ጀምሮ ማህበረሰቡን ያነሳሳበት መንገድ ሀሰተኛ መረጃን በማሰራጨት ነው፤ በደርግ ጊዜም የእርዳታ እህሎችን እየሸጠ የአለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን ትግራይ ላይ ረሃብ ገባ እያሉ የሚዘግቡበት ጊዜም ነበር። ሀሰተኛ የሆነ መረጃዎችን የሚያስተላልፍባቸው በዚህም ዓለም አቀፉን ማህበረሰብ የሚያሳስተው አንዳንድ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም ነው። ይሄ አካሄዱ ደግሞ ቀደም ሲልም የሚታወቅ አሁንም የቀጠለበት ነው።

ጫካ በነበረበት ወቅትም በራሱ ልሳን የሚያስተላልፈውም የሀሰት ትርክቶችን ፤ በህዝቦች መካከል የታሪክ መጣረስን በመፍጠር የማጋጨት ስራን ነበር። የሚገርመው አለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃንን በማጭበርበር ከዚህ ቀደም ከህዝብ በዘረፈው ገንዘብ ባለሙያዎችን እየገዛ በሀሰት መረጃ እንዲያሰራጭ የማድረግ ስራን ይሰራ ነበር።አሁንም የቀጠለው በነበረው በሚታወቅበት ታሪኩ ነው።

አሁንም አንዳንድ የውጭ መገናኛ ብዙሃን



ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠ



አቶ እንግዳወርቅ ታደሰ

የሀሰት ወሬውን እንዲቀባበሉት የሚያደርጉለትን ሰዎች በተቋማት ውስጥ በአስፈላጊ ቦታዎች ላይ በማስቀመጥ ፤ለማጭበርበር በዝርፊያ ያከበቱትን ገንዘብ እየተጠቀሙበት ነው። ለምሳሌ የኢትዮጵያ መንግስት የሰላም ጥሪ አድርጎ ለድርድሩ ኮሚቴ መዋቀሩን እነማን እንደሆኑ ጭምር ሲያሳውቅ አለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን አልዘገቡም ነበር። ህወሓት ግን የሆነች ነገር ከተነፈሰ የአለም መነጋገሪያ ያደርጓታል ። ይሄ የሚያሳየው መገናኛ ብዙሃኑ ለሙያ ያደሩ ሳይሆን በጥቅም የተያዙ መሆናቸውን ነው።

እነዚህ ቡድኖች የእነሱ ጉዳይ አለም አቀፍ ወሬ እንዲሆን በየቦታው ያስቀመጧቸው፤ ተከፍሏቸው የሚሰሩ ተቋማትና ግለሰቦች በመኖራቸው ይህ ሁኔታ እንዲፈጠር ማድረጉን ይናገራሉ። የቡድኑ አንዱ እስትራቴጂ ውሸትን ደጋግሞ በማሰራጨት እውነት ማስመሰል ነው። በዚህም የማህበራዊ መገናኛ ብዙሃንን ብሎም አንዳንድ አለምአቀፍ ሚዲያዎችን በጥቅም በመግዛት ለመቆጣጠር የቻሉበት ሁኔታ መኖሩን ያብራራሉ።

ጋዜጠኛ ጥበቡ እንደሚሉት፤ የኢትዮጵያ ህዝብ በአሸባሪው ህወሓት ውሸት ከአሁን በኋላ አይታለልም። የአለም ማህበረቡም ቢሆን ቡድኑ እንደልባቸው የሚጋልቡት ፈረስ ሆኖ ተመቻችቶ ስለተቀመጠላቸው አምነው የተቀበሉት ያስመስላሉ። ዋናው ዓላማቸው ግን ህወሓት የእነሱ መጠቀሚያ ስለሚሆን ይሄንን ቡድን ላለማጣት የፈጠራ ወሬዎችን በማሰራጨት ይተባበሩታል።

ወደትግራይ የሚላከው የሰብአዊ እርዳታ ለህዝቡ እንደማይደርሰው መንግስት እያወቀም ትርፍራፊውም ቢሆን ለትግራይ ህዝብ ይድረስ በማለት የእርዳታ እህል ወደ ክልሉ እንዲገባ ሲፈቅድ፤ እነሱ ለወታደሮቻቸው ቀለብ ብሎም ወታደራዊ ግብአት መግዣ እያደረጉት ይገኛሉ። አለም አቀፍ ሰብአዊ እርዳታዎች በሙሉ ወደ ጦር ካምፕ ይገባሉ። እርዳታ የጫኑ መኪኖች አይመለሱም። ስለዚህ ግን አንድም አለም አቀፍ ማህበረሰቡ ሲጮህ አይሰማም።

የተለያዩ የአለም አቀፍ ተቋማት ልኡካን በእርዳታ ስም ወደ ክልሉ ሲገቡ አለምአቀፍ የቴሌፎን ጥሪዎችን በመስጠት በማስደወልና በማገናኘት ድጋፍ ሲሰጣቸውም ታይቷል። ይህንንም አይዘግቡትም። አማራ ክልል የተፈፀመውን ወንጀል፤ አፋር ክልል ውስጥ የተፈፀመውን ጥፋት ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመቶች አልተዘገቡም። በየክልሉ የተደፈሩ ሴቶች፤ ህፃናትና አረጋዊያንን ጥቃትም ሲናገሩ አይሰማም።

ይህንን የሽብር ሀይል ትንፋሽ ለመስጠትና እድሜውን ለማራዘም የሀሰት ወሬውን መቀባበልን ልማዳቸው አድርገውታል ሲሉ ይናገራሉ።

ሌላው አስተያየታቸውን የሰጡን የወሎ ዩኒቨርሲቲ የጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ትምህርት ክፍል መምህር አቶ እንግዳወርቅ ታደሰ እንዳሉት ፤ የመገናኛ ብዙሃን ሙያ የራሱ የስነ ምግባር መመሪያዎች አሉት። ጋዜጠኝነትም ራሱ የሚመራበት በርካታ መመሪያዎች ሊኖሩት ይገባል። በውጭ መገናኛ ብዙሃን ላይ የምንመለከተው የሀገራቸውን ርዕዮተ አለም ተከትለው ከመሄድ ያለፈ ነፃና ገለልተኛ ናቸው ለማለት የማያስደፍር ነው።

እነዚህ መገናኛ ብዙሃን የሀገራቸውን ጥቅም እስካከበረ ድረስ የሙያውን ስነ ምግባር ስለመከተል ሲያስቡ አይታይም። ለምሳሌ የፌስ ቡክ ካምፓኒ “ ሞት ለራሺያ” ተብሎ መፃፍ ይቻላል ብሎ እስከ መፍቀድ የደረሰ ከስነ ምግባር የወጡ አስተሳሰቦችን ሲያራምዱ ይታያሉ።

አንዳንድ የምእራባውያኑ መገናኛ ብዙሃንም በሀገራቸው የሙያውን ስነ ምግባር በተወሰነ መልኩ ተከትለው እንደሚሰሩ ይታወቃሉ ፤ ነገር ግን በውጭ ሀገራት ጉዳይ በተለይም በአፍሪካ ላይ የሚሰሩት ዘገባዎች ንቀት የተሞላበት፤ መሬት ላይ ያለው ነገር ሳይጣሩ፤ እነሱ የሚፈልጉት አካል ያቀረበላቸውን መረጃ አግንኖ የማቅረብ አዝማሚያ ይታይባቸዋል ብለዋል።

እነሱ የማይፈለጉትን ወገን ደግሞ ይመታልናል፤ ያንቋሽሽልናል ብለው የሚያስቡትን ትኩረት ሰጥቶ ሲሰሩ ይታያል። ይህ ግን የሙያውን ስነ ምግባር የተከተለ አለመሆኑን ያሳያል። መገናኛ ብዙሃኑ ነፃና ገለልተኛ ሆነው እውነተኛ መረጃዎችን እንዲያሰራጩ ቢፈጠሩም፤ በጊዜ ሂደት ያ አስተሳሰብ ጠፍቶ የሀገራትን ጥቅም ብቻ እያስከበሩ ቀጥለዋል።

በምስራቅ አፍሪካ ባለው ሁኔታ አንድ ጠንካራ ሀገር ሳይሆን በግጭት እየተቆራቆዙ የምእራቢያዊያን ፍላጎት የሚያስፈፅሙ የተለያዩ አገራት እንዲኖሩ ይፈለጋል። ይህንን ደግሞ በሚዲያዎቻቸው ሲያንጸባርቁ ይታያሉ። እነሱ ፍላጎታቸውን ለማስፈፀም ቢነሱ አይደንቅም ያሉት አቶ እንግዳወርቅ፤ ይልቁኑ አፍሪካውያን ሀሳባችን መሆን የሚገባው ይሄንን እንዴት መቅረፍ እንችላለን የሚለው ነው ብለዋል።

አቶ ጥበቡ በመፍትሄነት የጠቆሙት ደግሞ፤ሀሰተኛና የተዛቡ መረጃዎችን የሚያወጡና የሚያሰራጩ መገናኛ ብዙሃንን መቋቋም የሚቻለውና እውነታውን ለአለም አቀፉ ማህበረሰብ ማስገንዘብ የሚቻለው ሀሰቱን ከእውነት ለይተው የሚያወጡ ተቋማትን ማጠናከር ሲቻል ነው። በእነዚህ በኩል ዜናዎች እውነት ወይም ሀሰት መሆናቸው ይረጋገጣል። እነሱም ሀሰተኛ ዜናዎች ሲወጡ ወዲያው በሳተላይት ፎቶግራፎች በማሳየት በተለያየ መልኩ እውነታን ያረጋግጣሉ። ሀሰቱንም ያጋልጣሉ።

በመገናኛ ብዙሃን የወጡ ዜናዎችን በመመልከት ውሸት ሀሰት ከማለት የሚበልጥ ስራ መስራት ይጠበቅባቸዋል። ይህ ሲባል ስለ እያንዳንዱ ጉዳይ በቂ መረጃንና ማስረጃን ይዞ በሀቅ ላይ የተደገፈ ዘገባ ማሰራጨት ተገቢ ነው። በሌላ በኩል ሀሰተኛ ነገሮችን መንግስት እራሱ ብዙ ተከታይ ባላቸው ሚዲያዎች ሀሰተኛ ዜና ይዘው የወጡትን ተአማኒነታቸውን ማሳጣትና ማጋለጥ አለበት።

ሚዲያው የሚገኝበት ሀገር ያሉ የኢትዮጵያን ህዝብ የወከሉ አምባሳደሮች፤ ዲፕሎማቶች ይሄንን ሀሰተኛ መረጃ መታገል አለባቸው። ዲፕሎማቶች ከሀገራቸው ብዙ ገንዘብ እየተከፈላቸው ለሀገራቸው ሲቆረቆሩና ሲታገሉ አይታይም ይሄንን ማስቀርት ግዴታ መሆን አለበት ።

ዲፕሎማቶቻችን በማህበራዊ ትስስር ገፃቸው ይሄንን መታገል ይገባቸዋል። በተጨማሪም ሀሰተኛ ዜና ያሰራጨውን የሚዲያ ተቋም መጠየቅ አለባቸው። ልክ እንደ ባዶ ቤት ትቶ ዝም ከማለት ሉአላዊት ሀገር መሆኗን በሚያሳውቅ ልክ ሁሉም የሀገሪቱ ህዝብ ተናቦ መስራት ይኖርበታል። የሀገሪቱ መገናኛ ብዙሃንም በሀገር ጉዳይ በጋራ በመሆን ምርመራ በማድረግ ዘገባቸውን መስራትና ማጋለጥ ይኖርባቸዋል ብለዋል።

አቶ እንግዳወርቅ በበኩላቸው፤ የሀገር ውስጥ መገናኛ ብዙሃን የሆነ ነገር ሲከሰት ለዛ ምላሽ የሚሰጡ ብቻ መሆናቸው ችግሩ እንዲበባስ አድርጎታል ይላሉ። ይህ ሲባል መገናኛ ብዙሃኑ ቀድመው አጥንተው በአካባቢው የሚገኘውን ተጨባጭ እውነታ ማሳየት አለባቸው። በዚህ ላይ በእቅድ ተይዞ የሀገሪቱን ሉአላዊነት ያስጠበቀ ዘገባ ቢሰራ በተሻለ መልኩ የሀገር ጥቅም ይከበራል።

በሀገራችን በተለይ በእንደዚህ አይነት በጦርነት ወቅት አንድ አይነትና የተናበበ መረጃ ማቅረብ የግድ ነው። የመንግስት የግል ጋዜጠኞች ተብለው በተዘበራረቀ መንገድ መሄዳቸው ቀርቶ እንደ ሀገር በአንድ አቋም የሀገርን ሉአላዊነት በሚያስከብር መልኩ መንቀሳቀስ የግድ የሚል መሆኑን ጠቅሰዋል።

በመንግስት በኩል ፈጣንና ተገቢው መረጃ ባለመስጠቱ በሌሎች በኩል የሚወጡ መረጃዎች እውነት እንዲመስሉ እየተደረገ ይገኛል። ይሄንን ለመቅረፍ የሚመለከታቸው አካላት በየጊዜውና በአግባቡ መረጃ መስጠት የግድ መሆኑን በመረዳት የተሟላ መረጃ በጊዜው መስጠት ይገባል።

እውነተኛ መረጃዎችን በተቀናጀ መልኩ መስጠት የሀሰት መረጃዎች እንዳይበዙ ያደርጋል። ከዚህም በላይ የሀገሪቱ ዋና ዋና መገናኛ ብዙሃን ችግር አለበት የተባለው ቦታ ድረስ በመሄድ ዘገባ እንዲሰሩ ጥበቃ መስጠት፤ የሚድያ ሰዎች መረጃ ሰብስበው እንዲያሰራጩ መፍቀድ የሀሰት መረጃን ለማስቆም የተሻለ አማራጭ መሆኑን አስረድተዋል።

ባለሙያዎቹ እንዳሉት፤ አንዳንድ ዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሃን በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ የተዛባ መረጃ የሚያወጡትና ሀሰተኛ ዘገባ የሚያቀርቡት ከህወሓት ጋር ባላቸው የጥቅም ትስስር፤ በምስራቅ አፍሪካ ኢትዮጵያ ጠንክራና ጎልታ እንዳትወጣ ባላቸው ፍላጎት ነው።ይሄንን መቋቋም የሚቻለውና የኢትዮጵያን እውነት ወደፊት ማምጣት የሚቻለው ሀሰተኛ ዘገባዎችንና የዘገቡትን መገናኛ ብዙሃን በመረጃና በማስረጃ ማጋለጥ ሲቻለ ብቻ ነው። ለዚህም ሀሰተኛውን ዘገባ የሚያጋልጡ ተቋማትን ማጠናከር ያስፈልጋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# የመስቀል በዓልና ሴቶች

**ሰላማዊት ውቤ**

መስቀል በዓል ከአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ማለትም ንግሥት እሌኒ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትን መስቀል አስቆፍራ ካስወጣችበት ጊዜ ጀምሮ በእምነቱ ተከታዮች ዘንድ በድምቀት ይከበራል:: ንግሥቲቷ መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ ቂራቆስ በተባሉ አባት ጠቋሚነት ለማግኘት ደመራ አስደምራ ፍለጋ የጀመረችው መስከረም 17 ቀን እንደሆነ የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ:: ይህ ደግሞ የሴቶች ተልእኮ ከአከባበሩ የሚጀምር እንደሆነ የሚያረጋግጥልን ነው:: ምክንያቱም በሴቶች መሪነት መስቀል ታሪክ ሆኗል::

በዓሉ ሃይማኖታዊ ይዘትን ይዞ በየአካባቢው ማኅበረሰብ ባህልና ወግም ሆኖ እንዲከበር በር ከፍቷል:: ከዚያም ሻገር ብሎ ዓለም እንዲያውቀውና በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) የማይዳሰሱ ቅርሶች ሆኖ ሊመዘገብ ችሏል:: ይህ ደግሞ ለአገር ገቢ እስከመሆን የሚያበቃውን ታሪክ በሴቶች እንደተሰጠው ይነግረናል::

በዓሉ በድምቀት ከሚከበርባቸው አካባቢዎች ብንነሳ ቅድሚያ ወደ አዕምሯችን የሚመጣው ጉራጌ እንደሆነ ሁላችንም እንስማማበታለን:: በዚህም መሰረት ዛሬ ከአዲስ አበባ 215 ኪሎ ሜትር ተጉዘን ጉራጌ ምድር ላይ እንከትማለን:: በምን ካላችሁ በሀሳብ ነው:: ስለዚህም በዚህ ሆነን ያንን እንቃኘዋለን:: እንደ ንግስት ኢሌኒ ለበዓሉ መሰረትና ድምቀት የሆኑትን ሴቶች እናነሳለን:: የሴቶችን የመስቀል ዝግጅት፤ ልፋትና ደስታ እንዲሁም አጠቃላይ ሁኔታ በአዲስ አበባ ቢሆኑም ባህሉን እየኖሩ፤ ሌሎችን እያደመቁ ያሉትንም በማነጋገር ነው ሁኔታውን የምናወሳላችሁ::

ያው እንደምታውቁት አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ መዲና ነች:: ስለዚህም የማይኖርባት ማህበረሰብ የለም:: በባህሉ የማይደምቅባት ሰውም እንዲሁ:: ስለሆነም መስቀልና ሴቶችን ለማንሳት መገናኛ አካባቢ ባለው በአደብና ሆቴል ተገኝተናል:: ስንገባ ያገኘናት መጀመሪያ ወጣት ሲሳይ ሞንሹን ነው:: መስቀል የጉራጌ ብሔረሰብ ልዩና አውራ በዓሉ እንደሆነ ታነሳለች:: ጉራጌ ቡልቡላ አካባቢ የተወለደችው ወጣቷ ለሥራ ወደ አዲስ አበባ ከመጣች ብዙ ጊዜ ቢሆናትም ባህላዊ ምግቦችን የዘወትር ሥራዋ አድርጋ ቀጥላለች:: ለዚህ ደግሞ መስቀልን ለማክበር ወደ ሀገር ቤት በየጊዜው መሄዷ ጠቅሟታል:: ባህሉን ከነስርዓቱ ሁልጊዜ የመተግበር ልምድም አላት::

እንዳጫወተችን በዓሉን ለማክበር ስትሄድ ልብስ ፤ ጨው፤ ስኳር ፤ ለአባቶች ጠርሙስ አረቄን ጨምሮ እንደ ማንኛውም ከሀገር ቤት ለሥራ እንደወጣ የጉራጌ ልጅ ለወላጆቿ ይዛ ትሄዳለች:: ሴትም ሆነች ወንድ ይሄን ማድረጋቸው የማይቀር እንደሆነም ታስረዳለች። ኖራትም አልኖራትም ለበዓሉ የግድ ሀገር ቤት መሄድ አለባት። ካልሄደች እርግማን ስላለው በጣም መጥፎ ነው። ወላጆቿ አፍ አውጥተው ባይረግሟት የሌሎች ልጆች ሲመጡ ሲያዩ እሷ በመቅረቷ ያዝኑባታል። ስለሆነም ሁልጊዜ መስቀልን ከቤተሰቦቿ ጋር ታሳልፋለች::

ወላጆቿ ብቻ ሳይሆኑ ጎረቤትም ይጠብቃታል። ሴት ስለሆነች በክትፎ ከተፋውና በበዓል ሥራዎች ሀገር ቤት ካሉት ሴቶች ጋር መሥራትና ማገዝ ይኖርባታልና ያ እንዲያልፋት አትፈልግም። በእርግጥ በባህሉ ዘንድ እንግዳ ናት ብሎ ዝም የሚላት የለም። « የቄስና የሴት እንግዳ የለውም» አይደል የሚባለው:: እዚህም እንዲያው ነው:: ይህ ባይሆን እንኳን እሷ ምርቃቱን ስለምትፈልገው በረከቱን በማሰብ ከሥራ ወደኋላ አትልም::

ሲሳይ እንደምትለው፤ በተለይ ገጠር ያሉት ሴቶች ለወዲያኛው መስቀል በዓል ዝግጅት የሚጀምሩት የዚህኛው መስቀል እንደወጣ ነው። ፈጥነው በየግላቸው ከሚያጠራቅሙት ቅቤ በተጨማሪ በየአካባቢያቸው የቅቤ ዕቁብ ይገባሉ። ከየአካባቢው የሚመጡትንና በሥራ የሚያግዟቸውን ሴቶችም ሆነ ተወላጆች በሙሉ የሚጠብቋቸው ተዘጋጅተው ነው። በዓሉ ሳምንት ሲቀረው ቅቤው ይነጠራል። ዘንድሮ የተፋቀ ቆጮ ለዘንድሮ መስቀል ስለማይሆንም ቆጮ መፋቅ የሚጀምሩትም የዚህኛው መስቀል እንደወጣ ነው። ይቆረጥና ዓመት ሙሉ ታፍኖ ይቀመጣል። መስቀል ሊደርስ ሁለት ወር ሲቀረው በመጭመቅ ወደ ዝግጅት ይገባሉ።

ታፍኖ ረጅም ጊዜ የሚቆይበት ምክንያቱ ጣዕም እንዲኖረው ለማድረግ ነው።ለምሳሌ፡- ለዛሬ መስቀል ቆጮ መሥርያ የተጠቀምነው አምና ያዘጋጁትን ነው:: የቡላም ዝግጅት ተመሳሳይ ነው። በነገራችን ላይ ጉራጌ ላይ ወድቆ የተሰበረ ሰው ሴቶች በቅቤ ያበደ የቡላ ገንፎ እየሰሩ ስለሚመግቡት ሁለት ወር ሳይቆይ ከስብራቱ ይጠገናል:: በአጠቃላይ በበዓሉ ምክንያት በሴቶች ላይ የሚደርሰው የሥራ ጫና ከፍተኛ ነው። ነገር ግን እሷን ጨምሮ ሁሉም ሴቶች ደስታ እንጂ ቅሬታ አይሰማቸውም። ምክንያቱም ያዘጋጁትን ክትፎም ሆነ ምግብ የሚመገበው ሁሉ ይመርቃቸዋል::

የሶዶ ጉራጌዋ ወይዘሮ የኔነሽ ታዬ እንዳወጉን ደግሞ፤ በጉራጌ የሴቶች ተብሎም መስቀል በልዩ ሁኔታ ይከበራል። የዚህ በዓል ወጪ በሙሉ በሴቶች ነው የሚሸፈነው። ሆኖም ይሄ በዋናው መስቀል በዓል ሴቶች ከጉልበት ውጪ በገንዘብ የሚያደርጉት አስተዋጾ የለም ማለት አይደለም። በዓላቸው የሚከበረው መስከረም 14 ሲሆን፤ በዕለቱ ሴቶች በልዩ ሁኔታ በራሳቸው የሚዘጋጀውን የጎመን ክትፎ የሚያቀርቡበት ነው:: ለማባያ የሚውል ቅቤ በዕቁብም ሆነ በሌላ መንገድ ማጠራቀም የሚጀምሩትም ነው:: ምክንያቱም በሴቶች እንደ ክትፎ ሁሉ ድቅቅ ተደርጎ የተከተፈው ጎመን ከሥጋ ክትፎ ባልተናነሰ ብዙ ቅቤ ይወስዳል።

የሚከተፈው ጎመን ብዙ በመሆኑ ሴቶች እንደ ሥጋው ክትፎ ሁሉ በየአካባቢው ተሰባስበውና ተጠራርተው በሕብረት ያደርጉታል:: ስለዚህም ይህ ቀን ለእነርሱ መሰባሰቢያቸውም ነው:: የመስቀል በዓል ሥራ ለሴቶች እጅግ አድካሚ ነው። ቆጮ ቆረጣና ጨመቃው ቀርቶ ወደ ምግብ ዝግጅቱ ከተገባ በኋላ ያለባቸው የሥራ ጫና በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም:: ለምሳሌ ከአምቾ የሚወጣውን ተንጣሎ የቀረውን ቡላም መለየት አንዱ ነው። ሆኖም ይሄ ሁሉ ድካም ልዩ በሆነው የበዓሉ ድባብ ተኖ ይጠፋል:: በሳቅና ጨዋታው ፤ጭፈራው እንዲሁም በምግብና መጠጡ ሲሳተፉ ይረሱታል ይላሉ።

ለሥራ አዲስ አበባ መጥተው ለመስቀል በየዓመቱ ሀገራቸው በመሄድ የሚያከብሩት ወንድ የጉራጌ ተወላጆችም የመስቀል በዓል ሴቶችን የበለጠ እንደሚያደክም አይክዱም። ወጣት ሙሉጌታ ገብሬ አንዱ ሲሆን፤ ለበዓሉ ለመሄድ ቸኩሎ ቢሆንም ስለሴቶች የሥራ ጫና እንዳጫወተን፤ የተወለደው አሁን ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ከሚገኝበት አካባቢ 20 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ኢዣ አገና በተሰኘ ከተማ ነው። በየዓመቱ የሚሄደው የቤረሰቡ ተወላጅ ያልሆኑትን ሁለት ሦስት እንግዶች ይዞ ነው። ለሦስት ቀን ብለው ሄደው መብላት መጠጣቱና ከቤተሰባቸው ጋር መገናኘቱ ስለሚያስደስታቸው 15 ቀን ይቆያሉ:: እናም በዚህ ቆይታቸው ሁሉም የሚመገቡትን ከቀን እስከ ሌት የሚያዘጋጁት ሴቶች እንደሆኑ ይመሰክራል::

አብዛኛው የጉራጌ ተወላጅ መንደሮች ይራራቃሉ። ሆኖም መቀራረብና አብሮ በዓሉን ማሳለፍ ግድ ነው:: በዚህም በባህሉ ሊስትሮም ቢሆን እየጠረገ ለእናት አባቱ ለመስቀል መዋያ ገንዘብ አጠራቅሞ የመጣው ተወላጅ ሁሉ እነዚህን ቤተሰቦችና ጎረቤቶቹን በሙሉ እየዞረ መጠየቅ ግዴታው ነው። በዞረበት ሁሉ ይበላል ይጠጣል፤ የቻለውን ያደርጋልም። የዚህ ጊዜ ደግሞ የሴቶች ልፋት እጅጉን ይጨምራል:: ምክንያቱም እንግዳ የሚበዛበት ወቅት በመሆኑ የተሰራው ባይበቃ እንኳን ዳግም መስራት ግዴታ ይሆንባቸዋል:: ሥጋ መፍጫ የገባባቸው ዘመናዊ አካባቢና ነዋሪዎች ቢኖሩም ሴቶች ክትፎውን በእጃቸው ነው የሚከትፉት። ስለዚህም የእነርሱ ውሎ የሚሆነው ክትፎዎቹ ሲሰሩ፤ ቅጠሉ ላይ ተጨልፎ ከተደረገ በኋላ ቅቤ ሲያፈሱ፤ ቤተዘመዱን ሲያስተናግዱ ነው::

ሌማት ሪስቱራንትና ባር ሥጋ ቤት ሥጋ ሻጩ ምህረት ሳህሌ እንደሚለው ደግሞ፤ መስቀል ለጉራጌ መገናኛው፤ ሀሳቡን መግለጫው፤ የሕይወቱን ምሶሶ ማቆሚያው ነው:: አከባበሩ የሚጀምረው ከመስከረም 12 ሲሆን፤ እስከ ጥቅምት 5 ድረስ ይቆያል:: በዚህ ውስጥ ታዲያ ሴቶች ከበዓሉ ዝግጅት ጀምሮ በልዩ ሁኔታ የሚያከብሯቸው ዕለቶች ይለያሉ:: ምክንያቱም ለበዓሉ ዝግጅት ሲደረግ ሥራ በጾታና በዕድሜ ይከፋፈላል:: እናም ሴቶች ለሚመጣው መስቀል በዓል የሚሆን ቅቤ ማጠራቀም አንዱ ተግባራቸው ተደርጎ ይሰጣቸዋል:: የወራት ዝግጅታቸው ቤት ማሳመርንም ያካትታል:: በዓሉ ሦስት ወራት ሲቀሩት መሰናዶውም ይጧጧፋል:: በተለይም ወጣት ሴቶች ቤት ቀለም መቀባት ጭምር ይሰራሉ:: ስለዚህም የቡሔ በዓል ከተከበረ በኋላ የመሰናዶውን ፍጥነት በየጊዜው እየጨመሩ ነው የሚሄዱት::

የጉራጌ ሴቶች የመስቀል በዓል መከበር በሚጀምርበት መስከረም 12 ቀን ለምግብ ማቅረቢያ የሚውሉ ቁሳቁሶችን ከግርግዳ ያወርዳሉ:: ዕለቱ ‹‹ሌማት የሚወርድቦ ቀን›› በመባል የሚታወቅ ሲሆን፣ በዕለቱ የመመገቢያ ቁሳቁሶች እንዲሁም ቤት ይፀዳል:: በየቤቱ አዳዲስ ጅባዎች ይነጠፋሉ:: ቀጣዩ ቀን ‹‹ወሬት ያሸና ወይም ወልቀነ›› የሚባል ሲሆን፤ ሴቶች የጎመን ክትፎ የሚያዘጋጁበት እለት ነው:: እናም ከቆት የሚበላበት ዕለት በመባል ይታወቃል::

ሌላው በጉራጌ ባህል መስከረም 14 የሚከበረው ደንጌሳት የሚባለው ቀን ሲሆን፤ የጎመን ክትፎ በሸክላ ጣባ ለመላው ቤተሰብ የሚቀርብበት ዕለት ነው:: በዕለቱ የሚወጣውን ወጪ በሙሉ የሚሸፍኑት ሴቶች ናቸው:: ሴቶች ዓመቱን በሙሉ ለመስቀል ባጠራቀሙት ገንዘብ ሙሉ ዝግጅቱን ሸፍነው ቤተሰባቸውን ያስተናግዳሉ:: በደንጌሳት ማታ በየቤቱ ደመራ ይለኮሳል:: ሥርዓቱ የባዮፕ ኸሳት ቀን ይባላል:: ደመራው ሲቃጠል ሴቶች እልልታ ያሰማሉ:: ለበዓሉ በሰላም በመድረሳቸውም ፈጣሪን ያመሰግናሉ::

መስከረም 18 ሲደርስ ደግሞ ሴቶች የተለያዩ የስፌት ቁሳቁሶች ለማዘጋጀት የሚውል ስንደዶ መልቀም ይጀምራሉ:: ይህ ቀን የፊቃቆማይ ይባላል:: የአካባቢውን ባህላዊ ዜማ እያሰሙ ስንደዶ የሚለቅሙበት ጊዜ ነው:: ከመስከረም 17 እስከ መስከረም23 ያለው ደግሞ የጀወጀ ወይም የጀወቸ አማች መጠየቂያ ጊዜን ያከብራሉ:: በዚህ አማች መጠየቂያ ወቅትም ሴቶች ለእናቶቻቸው የፀጉር ቅቤ፤ ለአባቶቻቸው ባርኔጣና ጭራ ይገዛሉ:: ባሎቻቸው ደግሞ ሙክት ይሸምታሉ:: ወቅቱ ልጆች በወላጆቻቸው እንዲሁም ባለትዳሮች በአማቾቻቸው የሚመረቁበትም ነው::

የመስቀል በዓል አከባበርን ከሚያጎሉ ሥርዓቶች መካከል የአዳብና ባህላዊ ጭፈራ ሥነ ሥርዓት ተጠቃሽ ነው:: አዳብና ከመስከረም 16 ቀን እስከ ጥቅምት 5 በዓል ባሉት ቀናት ይከናወናል:: ከተማ ይቀበልህ፤ ቀና ይሁንልህ፤መንገድ ይክፈትልህ። ለሰው መልካም ሁን። ይስጥህና ለሰፈሩ ሕዝብ ለሁሉም መግብ ተብሎም በእናትና አባቶች ይመረቅና ወደየመጣበት ይበተናል። ሀገር ቤት የቀሩ ሴቶች በፊናቸው ወዲያው ለቀጣዩ መስቀል ቆጮ ዝግጅት እንሰት መረጣ ይሄዳሉ። እኛም ምርቃታቸው ደርሶን አገራችንን ሰላም ያድርግልን በማለት ለዛሬ ተሰናበትን:: መልካም በዓል!



በመስቀል በዓል የሴቶች መስተንግዶ

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ከ60 ዓመት በፊት የታተሙትን የአዲስ ዘመን ጋዜጦች ስዓምዳችን አቅርበናል:: በውጋዴን የሚንቀሳቀሱ ሽፍቶችን ስማስወገድ በዘመኑ የነበሩ ባላባቶች ያደረጉትን ምክክር ቃኝተናል፤ በዘመናችን በየቦታው የሚታየውን የጀሌዎቹናና የጆሌዎቹ ‹አኩይ ጽንፈኛ ተግባር ፤ በየአካባቢው ያሉ አመራሮችና የፀጥታ ጥበቃ አባሉች በንቃት ተመካክረው አውዳሚ ተግባራቸውን ስመቆጣጠር ፕረት ማድረግ እንዳስባቸው ያሳየናል:: የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት የነበሩት የመቶ አለቃ ግርማ ወልደጊዮርጊስ በ1956 ዓ.ም የሕግ መምሪያ ፕሬዚዳንት ሆነው እያገለገሉ ሳለ በዮጎዛላቪያ በተካሄደው የኢንተር-ፓርላማ ጉባኤ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው መመረጣቸውንና ባደረጉት ንግግር አፍሪካውያን የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው ስመወሰን የሚያደርጉትን ፕረት አድንቀዋል:: ከዘመናችን ጋር ስናስተያየው ሀገራችን ችግሮቻችን የሚፈቱት በአፍሪካ ኅብረት ነው ማስቷን እናደንቃስን፤ ሴሎችም ዜናዎች አካተናል::**

### ሽፍቶችን ስማስወገድ ፈቃድ ጠየቁ

ሐረር ፤ በውጋዴን ግዛት የሚገኙ ባላባቶች ሁሉ ከየጐሣቸው አንዳንድ ታላላቅ ባላባቶች ወደ ሐረር በመላክ ሽፍቶቹ በሀገራቸው ላይ ስለሚያደርጉት ጉዳት አሳባቸውን ለጠቅላይ ግዛቱ እንደራሴ ለክቡር ሌተና ኰሎኔል ታምራት ይገዙ እንዲገልጹላቸው አድርገዋል ፤ የተላኩት ባላባቶችም መስከረም ፫ ቀን ፲፱፻፶፮ ዓ.ም. ወደ ክቡር እንደራሴ ቀርበው የተሰጣቸውን እምነትና አደራ የረሱ ከሃዲዎች በሀገራችን ላይ በመሸፈት ሀገራችንን ከማጥፋት በላይ በንብረታችን ላይ ከፍተኛ ጉዳት ስላደረሱብን ተባብረን ለማጥፋት ቆርጠን የተነሳን ስለሆነ ፤ መንግሥታችን ይህንኑ እንዲፈቅድልን እንለምናለን ። ሽፍቶቹም ተወላጆቻችን አይደሉም በማለት አሳባቸውን ገልጸውላቸዋል።

ክቡር እንደራሴውም አሳባቸውን ካዳመጡ በኋላ ፤ ሰው ሆኖ የማያጠፋ የለም ፤ ቢቻል በምክር ውንብድነታቸውን ቢተዉ ምከሩአቸው ፤ ካልሆነ እያንዳንዳቸው እጃቸውን እየያዛችሁ ለመንግሥታችሁ ብታስረክቡ መልካም ነው ፤ በማለት መልስ ስለሰጡዋቸው ምስጋናቸውን አቅርበው ተመልሰዋል ። ከባላባቶችም የቀብሪ ደሐር አውራጃ ግዛት ሕዝብ እንደራሴ ቐኛዝማች አሙመር ባራሌ ፤ የቀላፎ አውራጃ ገዥ ቀኛዝማች በሽር ሴክ አብዲ ፤ የሬርሬር ወረዳ ግዛት አቶ መሐመድ ባሂር ሌሎችም እነሱን የመሳሰሉ ተገኝተው ነበር ሲል በጠቅላይ ግዛቱ የሚገኘው ወኪላችን አስታውቋል ።

**( መስከረም 5 ቀን 1956 ዓ.ም ከወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ )**

### ከጎርፍ ሙላት አዳኑት

ደብረ ማርቆስ ፤መስከረም ፯ ቀን ፲፱፻፶፮ ዓ.ም ከሁለት ሰዓት በፊት በጣለው ኃይለኛ ዝናብ ምክንያት ፤ ደብረ ማርቆስ ከተማ የሚገኘው ውስታ የተባለው ወንዝ ሞልቶ ዕድሜው ፲፪ ዓመት የሆነ ልጅ ከጓደኛው ጋር በወንዙ ዳርቻ እንደቆመ ፤ የውሀው ማዕበል ስለወሰደው ፤ ወታደር የሺጥላ አፍኔ የተባለ የፖሊስ ባልደረባ ፤ አደጋውን ተመልክቶ ባሳሰበው መሠረት ፤ የአካባቢው ሰው እንዲሰበሰብ አድርጎ የወንዙ ሙላት ልጁን ከ፴ ሜትር በላይ እያንገላታ ከወሰደው በኋላ ፤ የተሰበሰበው ሰው አጠናና ልዩ ልዩ ነገር በማቀበል ፤ልጁን ከውሀ ሙላት አደጋ ሊያድኑት ችለዋል።

**( መስከረም 9 ቀን 1956 ዓ.ም ከወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ )**

### የ ፶ አለቃ ግርማ ወ. ጊዮርጊስ በኢንተር- ፓርላማ ጉባኤ

የኢትዮጵያ የሕግ መምሪያ ፕሬዚዳንት የተከበሩ የ ፶ አለቃ ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ ለ፶፪ ኛው የኢንተር- ፓርላማ ጉባኤ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው ተመርጠዋል።

የተከበሩ የ ፶ አለቃ ግርማ ለጉባኤው ባደረጉት ንግግር ፤ዮጎዝላቪያ ስላደረገችላቸው መልካም አቀባበል ከአመስገኑ ና በእስኮፔጅ ስለደረሰውም አሰቃቂ ጥፋት የተሰማቸውን ቅሬታ ከገለፁ በኋላ ፤ « ብዙ የአፍሪቃ አገሮች የራሳቸውን ጉዳይ ራሳቸው ለመወሰን የሚያደርጉት አስደናቂ ጥረት ፤ለአፍሪቃውያን ራሳቸውን ለማስተዳደር አልበቁም የሚለውን መሠረተ ቢስ ሀሜት የሚያስተባብል ነው » ብለዋል ። እንደዚሁም የአዲስ አበባው ከፍተኛ ጉባኤ በአፍሪቃ ታሪክ ውስጥ አንድ ትልቅ ምዕራፍ መሆኑን አስገንዝበዋል።

የተከበሩ የመቶ አለቃ ግርማ ፤ስለ ኑክሊየር በመስኮብ የተደረገው ውለታ አንድ ጥሩ ውጤት መሆኑ ከገለጡ በኋላ ሌላው የሰላም አስጊ ጉዳይ ደግሞ የዘርና የቀለም ጉዳይ መሆኑን አሳስበዋል ።ፕሬዚዳንት ኬኔዲ የቀለምን ልዩነት ለመደምሰስ የሚያደርጉትን ጥረት የመቶ አለቃ ግርማ አመስግነዋል ።

የደቡብ አፍሪቃ ሁናቴ ከቀን ወደ ቀን እየተባባሰ መሄዱን በመግለጥ ፤ በደቡብ አፍሪካ መንግሥትና በፖርቱጋል አገዛዝ ሥር በሥቃይ የሚገኙት አፍሪቃውያንን ለማዳን የፓርላሜንት አባሎች ሁሉ የተቻላቸውን ያህል እንዲረዱ የመቶ አለቃ ጠይቀዋል ።

**( መስከረም 12 ቀን 1956 ዓ.ም ከወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ )**

### ስኩዩ አቦቴ ሰዎች በተስቦና ፈንጣጣ የነፃ ክትባት ተሰጠ

ፍቼ ፤በሰላሌ አውራጃ ግዛት በፍቼ ጤና አጠባበቅ ጣቢያ ሥራ የሚተዳደሩ የኩዩ አቦቴ ወረዳ ግዛት የገብረ ጉራቻ ወረዳ ግዛት ክሊኒክ ከመስከረም ፩ ቀን ሺህ ፱፻፶፭ ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጳጉሜ ፮ ቀን ሺህ ፱፻፶፭ ዓ.ም ድረስ በተመላላሽ ፩ ሺህ ፳፭ በተስቦ ክትባት ፤፩ ሺህ ፱፻፹፫ ፤ በፈንጣጣ ክትባት ፩ ሺህ ፪፻፲ ፤ በጠቅላላው ለ፯ ሺህ፪፻፷፰ ሰዎች የነፃ ሕክምና ማድረጉን የክሊኒኩ ኃላፊ አቶ ዘመድኩን በነበሩ አረጋግጠዋል ሲል ወኪለካችን ገልጿል ።

**( መስከረም 15 ቀን 1956 ዓ.ም ከወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ )**

### የፖሊሶች እርሻ

በገለብና ሐመር ባኮ አውራጃ የሚገኙ ፖሊሶች ከፀጥታ ጥበቃቸው ጋር ሕዝቡን ስለ እርሻ ጥቅም ያስተምራሉ ። ከዚህ ቀደም ባሳዩት የእርሻ አዝመራ አስደሳች የጤፍ ምርት አግኝተዋል ። ባለፈው ዓመትም እርሻቸውን በጥራጥሬ ዘር ሞክረውታል ። መሬቱም ፍጹም ድንግል በመሆኑ ፤አስደሳች የሆነውን ምርት አግኝተዋል ።

ሕዝቡም የፖሊሶቹን አርአያ በመከተል የእርሻን ሥራ እንደሚያስፋፋና የራሱን ኑሮ እንደሚያሻሽል ፖሊሶች ተስፋ ያደርጋሉ ።

**( መስከረም 6 ቀን 1956 ዓ.ም ከወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ )**

# ዓለም አቀፍ




## በኡጋንዳ የኢቦላ ወረርሽኝ እየተስፋፋ ነው

ከአንድ ሳምንት በፊት በበሽታው የተያዘ ግለሰብ በተገኘባት ኡጋንዳ በኢቦላ እንደተያዙ የሚጠረጠሩ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ ነው።የአገሪቱ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እንዳለው አስካሁን 34 በበሽታው የተጠረጠሩ ሰዎች እንዳሉ ሲገልጽ፣ 21 ሰዎች በኢቦላ ቫይረስ ሳይሞቱ አይቀርም ብሎ ያምናል።

የጤና ባለሙያዎች በበሽታው ከተያዙ ሰዎች ጋር ንክኪ ያላቸውን ለማግኘት ማፈላለጋቸውን እንደቀጠሉ ባለሥልጣንት ገልጸዋል። ወረርሽኙ የጀመረው በማዕከላዊ ኡጋንዳ ሙቤንዴ ወረዳ ቢሆንም ወደ ሁለት አጎራባች ወረዳዎች ተዛምቷል።

ነገር ግን በአገሪቱ ርዕሰ መዲና ካምፓላ በኢቦላ ተያዘ ሰው ስለመኖሩ እስካሁን የተረጋገጠ ነገር የለም።ኡጋንዳ የኢቦላ ወረርሽኝ ሲያጋጥማት ይህ ለአራተኛው ጊዜ ነው።ይህን ተከትሎ ጎረቤት አገራት በሽታው ወደ ግዛታቸው እንዳይዛመት በተጠንቀቅ ላይ መሆናቸውን ተናግረዋል።

እንደ ዓለም ጤና ድርጅት ከሆነ ኢቦላ በቫይረስ የሚተላለፍ በሽታ ሲሆን የመጀመሪያ ምልክቶቹም ድንገተኛ ትኩሳት፣ ከፍተኛ ድካም፣ የጡንቻ እና የጉሮሮ ቁስለት ናቸው።ይህ የበሽታው የመጀመሪያ ምልክት ሲሆን በመቀጠልም ማስታወክ እና ማስቀመጥን ጨምሮ አንዳንዴ ውስጣዊ እና ውጫዊ መድማት ያጋጥማል።

እንደ ቺምፓንዚ ያሉትን ጨምሮ ቫይረሱ ካለባቸው እንስሳትን ጋር ቀጥተኛ ንክኪ ሲኖር ቫይረሱ ወደ ሰዎች ይተላለፋል።ከሰዎች ወደ ሰዎች ደግሞ የሚተላለፈው በደም ንክኪ፣ ከሰውነት በሚወጣ ፈሳሽ እና በቫይረሱ ከተበከለ አካባቢ ጋር በሚኖር ግንኙነት ይተላለፋል።

በቫይረሱ ሕይወቱ ያለፈ ግለሰብ አስከሬን መንካትም ለቫይረሱ ያጋልጣል።ቫይረሱ ምልክት ለማሳየት ከሁለት እስከ ሦስት ሳምንት ሊፈጅበት ይችላል።ህክምናውም ቢሆን አስቸጋሪ የሚባል ነው።

በሽታው በአፍሪካ ተደጋግሞ ሲያጋጥም አንድ ጊዜ ደግሞ በፊሊፒንስ መከሰቱ ታውቋል።የዓለም ጤና ድርጅት ከኢቦላ ራስን ለመጠበቅ በሽታው ካለባቸው ሰዎች እና ከሰውነታቸው ከሚወጣ ፈሳሽ ጋር አለመነካካትን እንደ መፍትሔ ያቀርባል።

የጋራ መገልገያዎችንም አለመጠቀምንም ይመከራል።በበሽታው ከተያዙ ደግሞ ራስን በመለየት የባለሙያዎችን ድጋፍ መጠየቅ ይገባል።ሕክምናውን በደንብ በፍጥነት ከተከታተሉ ህሙማን የመዳን ተስፋ እንዳላቸው ቢቢሲ ዘግቧል።

## ፊሊፒንስን በመታው ከባድ አውሎ ንፋስ አራት የነፍስ አድን ሠራተኞች ሞቱ



ፊሊፒንስን የመታውን አውሎ ንፋስ ተከትሎ በተከሰተ ጎርፍ ምክንያት አራት የነፍስ አድን ሠራተኞች ሕይወታቸውን አጡ። ከከባድ አውሎ ነፋሱ በኋላ ጎርፍ የተከሰተ ሲሆን በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተቋርጦባቸዋል።ከርዕሰ መዲናዋ ማኒላ በስተሰሜን በሚገኘው ሳን ሚጌል አውራጃ በሥራ ላይ የነበሩ የነፍስ አድን ሠራተኞች ናቸው በድንገተኛ ጎርፍ የተወሰዱት።

አውራጃው በጎርፉ ክፉኛ ከተጠቁት መካከል አንዱ ሲሆን አንዳንድ ነዋሪዎች ቤታቸው ጣሪያ ላይ ለመሆን ተገደዋል።ኑሩ ተብሎ ስያሜ የተሰጠው አውሎ ንፋስ በሰዓት 240 ኪሎ ሜትር ይፈጥን ነበር ተብሏል። 110 ሚሊዮን ከሚሆነው የአገሪቱ ሕዝብ ግማሹ በሚኖርባትን ሉዞን ማጥቃቱም ታውቋል።

በአካባቢው ነዋሪዎች ካርዲንግ በመባል የሚታወቀው አውሎ ነፋስ መጀመሪያ ላይ ከባድ ነበረ ቢሆንም እሑድ ዕለት መቀዛቀዙ ተነግሯል። ሰኞ አመሻሽ ላይ ከፊሊፒንስ ይወጣል ተብሎ ይጠበቃል።በሳን ሚጌል አውራጃ ሳን ቪንሴንቴ በተባለች መንደር አንድ ሰው ውሃውን ከበሩ ለማራቅ ሲሞክር ታይቷል።

ሌላዋ በቤቷ ጣራ ላይ ቆማ የአገሪቱ መሪዎች "በአየር ንብረት ለውጥ ላይ ማተኮር አለባቸው" ስትል ጮክ ብላ ስትናገር ተደምጣለች።በመንደሩ የጎርፍ አደጋ ከጠዋቱ የደረሰ ሲሆን ውሃው እየቀነሰ መምጣቱ ተነግሯል።

ከ74ሺህ በላይ ሰዎች ከአውሎ ነፋሱ አካባቢ እንዲወጡ የተደረገ ሲሆን ባለሥልጣናቱ ቀደም ብለው በዋና ከተማዋ ማኒላ "ከባድ የጎርፍ አደጋ" ሊደርስ ይችላል ሲሉ ማስጠንቀቂያ ሰጥተዋል። እስካሁን ድረስ ከፍተኛ ጉዳት ወይም የሕይወት መጥፋት ስለመኖሩ የተገለጸ ነገር የለም።

የፊሊፒንስ ፕሬዝዳንት ፈርዲናንድ ማርኮስ ሰኞ ዕለት ባደረጉት ንግግር "ቢያንስ በዚህ ጊዜ ዕድለኞች ልንሆን እንችላለን ብዬ አስባለሁ። ባለፉት ሁለት ቀናት ካደረግናቸው ነገሮች መረዳት የሚቻለው ዝግጅት በጣም በጣም አስፈላጊ መሆኑን ነው" ሲሉም አክለዋል።

"እስካሁን ችግሩ አላበቃም። በሁለት እግር ቆመናል የምንለው አብዛኞቹ ተፈናቃዮች ወደ ቤታቸው ሲመለሱ ይመስለኛል" ብለዋል።ማርኮስ ግብዓቶች በአውሮፕላን እንዲላኩ እና ከፍተኛ ጉዳት ለደረሰባቸው የጽዳት መሣሪያዎች እንዲሰጡ አዘዋል።ከማኒላ በስተምሥራቅ በምትገኘው ክዌዘን ግዛት ዓሳ አስጋሪዎች ወደ ባሕር እንዳያመሩ ተከልክለው የነበረ ሲሆን አንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ መብራት ተቋርጦባቸዋል ተብሏል።

በተከሰተው አደጋ ምክንያት በረራዎች እና የጀልባ አገልግሎቶች ተሰርዘዋል። ፕሬዘዳንት ማርኮስ በሉዞን የሚገኙ ሁሉንም የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና ትምህርት እንዲዘጉ ማዘዛቸውን የዘገበው ቢቢሲ ነው፡፡

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾቻችንንና ፌስቡክ ገጾቻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ማክሰኞ ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## ታሪካዊ ውጤት የተመዘገበበት የበርሊን ማራቶን

ብርሃን ፈይሳ

በረጅም ርቀት ሩጫዎች ፈጣን ሰዓት ለማስመዝገብ እንዲሁም ክብረወሰንን ለማሻሻል ከፍተኛ ብቃትና ጽናት ያስፈልጋል። በዚህም ምክንያት አብዛኛውን ጊዜ አዲስ ክበረወሰን ለመስበር ረጅም ዓመታትን መጠበቅ የግድ ይሆናል። ጥቂቶች ግን በትልልቅ የውድድር መድረኮችና ብርቱ ተፎካካሪዎች ባሉባቸው ሩጫዎችም ጭምር አዲስ ሰዓት በማስመዝገብ በክብር ላይ ክብርን ይቀዳጃሉ።

የፕላቲንየም ደረጃ ከተሰጣቸው የጎዳና ላይ ማራቶኖች መካከል አንዱ የሆነው የበርሊን ማራቶን ደግሞ በተደጋጋሚ የዓለም ክብረወሰን ከሚመዘገብባቸው ውድድሮች መካከል ቀዳሚው ነው። በዓለም አቀፉ ቫይረስ ኮቪድ 19 ምክንያት አንድ ዓመት ከመቋረጡ በቀር ለ48 ዓመታት በተካሄደው በዚህ ማራቶን፤ በወንዶች ለ9 ጊዜያት፤ በሴቶች ደግሞ ለ3 ጊዜያት በርቀቱ የዓለም ክብረወሰን ተሰብሯል።

ለረጅም ዓመታት ኢትዮጵያውያንና ኬንያውያን አትሌቶች ብቻ የነገሱበት ይህ ውድድር ዘንድሮም አዲስ ፈጣን ሰዓቶች ተመዝግበውበታል። በሴቶች በኩል ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ባልተጠበቀ ሁኔታ የራሷንና የቦታውን ምርጥ ሰዓት ስታስመዘግብ፤ በወንዶች ደግሞ ከሶስት ዓመት በኋላ ኬንያዊው ብርቱ አትሌት የዓለም ክብረወሰንን በድጋሚ ከእጁ አስገብቷል።

ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ትዕግስት አሰፋ የቦታውን ክብረወሰን ከሁለት ደቂቃ በላይ በሆነ ሰዓት ያሻሻለች ሲሆን፤ የርቀቱን የመጨረሻ መስመር የረገጠችው 2:15:37 በሆነ ሰዓት ነው። ይህ ሰዓት ደግሞ ከኬንያዊቷ የክብረወሰን ባለቤት ብሪጊድ ኮስኬ (2:14:04) እና ለረጅም ጊዜ የርቀቱን ፈጣን ሰዓት የግሏ አድርጋ ከቆየችው እንግሊዛዊቷ ፓውላ ራድክሊፍ



ሦስተኛዋ የማራቶን ፈጣን አትሌት ትዕግስት አሰፋ፤

(2:15:25) በመቀጠል ሶስተኛው የርቀቱ ፈጣን ሰዓት በሚል ተይዞላታል። ኢትዮጵያዊያን የርቀቱን አትሌቶችም በፈጣን ሰዓቷ በቀዳሚነት የምትመራ አትሌት አድርጓታል።

የ28 ዓመቷ ወጣት አትሌት ትዕግስት አሰፋ 800 እና 4በ400ሜትር ርቀቶችን በመሮጥ የምትታወቅ አትሌት ስትሆን፤ እአአ የ2013 የአፍሪካ ወጣቶች ቻምፒዮና የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊም ነበረች። በ2016 ደግሞ የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮና እንዲሁም የሪዮ ኦሊምፒክ ላይም ብሄራዊ ቡድን ውስጥ ተካታ ሀገሯን መወከል ችላለች። እአአ ከ2018 ጀምሮ ደግሞ አትሌቷ ከመም ወደ ጎዳና ላይ ሩጫዎች የተሸጋገረች ሲሆን፤ በዚህ ዓመት የ10 ኪሎ ሜትር፣ የግማሽ እና የሪያድ ማራቶን ተሳታፊም ነበረች። በተደራራቢ ውድድሮች ላይ የቆየችው ብርቱዋ አትሌት ሜጀር በሚባለውና በርካታ ታዋቂ አትሌት ባሉበት በዚህ ውድድር ተካፍላ ብቃቷን ማስመስከር ችላለች።

ፈጣን በነበረው በበርሊኑ የማራቶን ሩጫ ላይ ስድስት የሚሆኑት አትሌቶች 1:08:13 በሆነ ሰዓት ርቀቱን ማጋመስ ችለዋል። 30 ኪሎ ሜትር ላይ ሲደርሱ ሰዓቱ 1:36:41 ሲሆን፤ ለአሸናፊነት ፉክክር ሲያደርጉ የነበሩት ደግሞ ሶስት ብቻ ነበሩ። እነርሱም ኢትዮጵያውያኑ አትሌቶች ትዕግስት አባያቸው እና መሰረት ጎላ ናቸው። ከ35 ኪሎ ሜትር ጀምሮ ደግሞ የርቀቱ አሸናፊ ትዕግስት አሰፋ ከሀገሯ ልጆች ጋር የነበራትን ልዩነት ወደ 20 ሰከንዶች በማስፋት ፈጣን ሰዓት በማስመዝገብ ጭምር ውድድሩን መፈጸም ችላለች።

ኢትዮጵያውያኑ አትሌቶች ተከታትለው በመግባት አሸናፊ ሊሆኑ እንደሚችሉ በሩጫው ወቅት ቢገመትም፤ ኬንያዊቷ አትሌት ሮዝሜሪ ዋንጂሩ 2:18:00 በሆነ ሰዓት በመግባት ሁለተኛ ደረጃን ልትይዝ ችላለች። በሩጫው ወቅት ከፍተኛ ግምት ያገኘችው ትዕግስት አብያቸው ደግሞ በሶስት ሰከንዶች ብቻ በመበለጧ ሶስተኛ ሆናለች። አትሌት ወርቅነሽ ኢዴሳ እና መሰረት ጎላም እስከ አምስት ያለውን ደረጃ መያዝ ችለዋል።

በወንዶች የማራቶን ንግስናን የግሉ ማድረግ የቻለው ኬንያዊው ኢሉድ ኪፕቾጌ ደግሞ በርቀቱ የራሱን ክብረወሰን በድጋሚ ማሻሻል ችሏል። የሁለት ጊዜ የኦሊምፒክ አሸናፊው ኪፕቾጌ ከ25 ኪሎ ሜትር አንስቶ ተፎካካሪዎቹን ጥሎ በመግባት አሸናፊ ለመሆን ችሏል። የገባበት የዓለም ፈጣኑ ሰዓትም 2:01:09 ሲሆን፤ የበርሊን ማራቶንን ለሶስት ጊዜያት በማሸነፍ የአራት ጊዜ ተከታታይ ባለድል ከነበረው ኢትዮጵያዊው ጀግና አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ ጋር ታሪኩን ለመጋራት ችሏል። አትሌቱ የርቀቱን ክብረወሰን በዚሁ ውድድር ላይ እአአ 2018 ላይ 2:01:39 በሆነ ሰዓት በመግባት ማስመዝገቡ የሚታወስ ነው።

ሌላኛው የሀገሩ ልጅ ማርክ ኮሪር አራት ደቂቃዎችን በመዘግየት በሁለተኛነት ሲገባ ያስመዘገበው ሰዓትም 2:05:58 ሆኗል። ታዱ አባቴ (2:06:28) እንዲሁም አንዱአምላክ በልሁ (2:06:40) ደግሞ ኬንያውያኑን ተከትለው በመግባት ሶስተኛና አራተኛ በመሆን ውድድሩን የፈጸሙ አትሌቶች ናቸው።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
Ethiopian Cooperative Commission
(ECC)
ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ የሚታተም

## የሰውና የእጽዋት መሰናሰል በተፈጥሮ ሚዛን

በአባቴነህ በየነ

ጥቅጥቅ ያለው ደን ለተመልካች አይን ምቹ ማረፊያ ሆኗል። በሌሊቱ ጀምረው ቀኑን ሙሉ መረዋ ዜማቸውን ሲያንቆረቁሩ ማድመጥ እና የጋራ መኖሪያቸውን ለመገንባት በኅብረት የሚረባረቡበትን ብርቅዬ አዕዋፋት መመልከት ለአዕምሮ ፍጹም ሰላም ይሰጣል።

በሀገር በቀል ዛፎች ጥቅጥቅ ካለው ደን ውስጥ የሚነፍሰው ቀዝቃዛ ነፋስ ከውድ ሽቶ የላቀ መዓዛን ይጋብዛል። ሰውም ሆነ እንስሳት የሚረማመዱበት የሳር ምድር በመልካም መዓዛ አፍንጫን ያውዳል። የጠዓመ አባይዳር ማህበረሰብ አንድ ዛፍ ከሚቆረጥ አንድ ሰው ቢሞት ይሻላል የሚል የጸና ዕምነት አለው። ማህበረሰቡ ችግኝ ሲረገጥና ሲቆረጥ ክፉኛ ይታመማል። የጥርስ መፋቂያ ለመቁረጥ እንኳን በምክንያትና በወጉ መሆን እንደሚገባው የትኛውም የአርሶ አደር አባል ይረዳል። ምክንያቱም ይህ ቦታ ለአባይ ወንዝ ትርታው፤ለሕዳሴው ግድብ የደለል ስጋት ህልውናው፤የቀጨም ወንዝና የዋነኞቹ የአባይ ወንዝ ገባሮች መነሻ፤እንዲሁም ከፍ ሲል ደግሞ ለጮቄ ተራራ የጀርባ አጥንት በመሆኑ ሕጻን አዋቂ ሳይባል ተፈጥሮን ይንከባከባሉ። የነገርኳችሁ አካባቢ በአማራ ክልል ደጋ ዳሞት ወረዳ የሚገኝ ሲሆን ተግባራቸው ያስደነቀኝ የጠዓመ አባይዳር አካባቢ ነዋሪዎች ነበሩ።

በዚሁ ድንቅ አካባቢ ተወልዶ ያደገውና በሰለጠነው አለም በርካታ የህይወት ልምድ ያካበተው አቶ አብይ አለም እንዲሁም ጀርመናዊት ባለቤቱ ወይዘሮ ባላሪ በተመለከቱት መልክአ ምድር በመደመም የሙሉ ኢኮሎጂን ሃሳብ ያመነጩና የተገበሩ በመሆናቸው በማህበሩ አባላትና በነዋሪው ማህበረሰብ ዘንድ ስማቸው በበጎ ይወሳል። የገነት ተፈጥሮ ሃብትና ቱሪዝም የኅብረት ስራ ማህበር ለሙሉ ኢኮሎጂ ህልውናው የመሆኑን ያህል የሎጁ ተኪ ይለሽ ጠቀሜታ



ለጠዓመ አባይዳር ማህበረሰብም ሆነ ለማህበሩ አባላት የጋራ ተጠቃሚነት መሰረት ለመሆኑ በጎ ተግባራቸው ገላጭ ሆኗል። ሰጥቶ የመቀበል ሚዛናዊ የተፈጥሮ መርህ የሰውና የዕጽዋት መሰናሰል በዚህ ሎጅ ይታያል።

በገነት የተፈጥሮ ሃብትና ቱሪዝም ኅብረት ስራ ማህበር ውብ ደን ውስጥ በሚገኘው ሙሉ ኢኮሎጂ ሲገኙ፤ በሀገር በቀል ዛፎች መንፈስዎን እያደሱ፤በሎጁ ፍጹም ተፈጥሯዊ አሰራር እጅግ እየተደመሙ፤በሚመገቡት ምግብ ተፈጥሯዊ ይዘት እየተደሰቱ ተጨማሪ ጊዜ ለመጠቀም ይገደዳሉ። የቤቶቹ አሰራር የባለ አንድ ፎቅ ጎጆ ሆነው በአካባቢው ተፈጥሯዊ ግብዓት የተገነቡ ናቸው። ከጣውላ የተሰሩት በሮች ማጠፊው ከመቃኑ እርስ በርሱ መሰናሰሉ ያስደንቃል። ወለሉ ከሚታወቀው የኢንዱስትሪ ውጤት ሳይሆን ከተፈጥሮ የቀርከሃ ተክል ውብ ስብጥር ተሰናድቶ በመነጠፉ ሲራመዱበት ከምቾቱ በላይ በአረማመድ ያቀናጣል። ከጭቃ የተሰራው ግድግዳ ዙሪያውን በአንድ ስንዝር ርቀት የተቀበሩት የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ጠርሙሶች ከተፈጥሮ ፀሐይ የተቀበሉትን ብርሃን ያለስስት በቀለማት ሞሽረው ከማጀት ያደርሳሉ። የገላ መታጠቢያ አገልግሎት ቢፈልጉ በሐረግና ቅጠላ ቅጠል ከለላነት በተዋበ የዛፍ ስር በነጻነት ይታጠባሉ። ፀሐይ እስክትጠልቅ የሞቀ ውሃ ተፈልጎ አይታጣም። የኅብረት ስራ ማኅበራት ተፈጥሮን በመንከባከብ በዘላቂ ልማታችን ላይ ያላቸው ሚና ገነት የተፈጥሮ ሃብትና ቱሪዝም ማሳያ ነው።

በሙሉ ኢኮሎጂ ከሁለትዮሽ ተግባራዊ የኅብረት ስራ ጽንሰ ሃሳብ ባሻገር በታዳሽ ኃይል አጠቃቀም የአካባቢ ጥበቃ ትኩረት ተሰቶታል። እዚህ አካባቢ ፀሐይ ከቀጥተኛ ሙቀቷ በላይ በተዘዋዋሪ የኃይል ምንጭ በመሆን ሕይወት አቅልላለች። የኅብረት ስራ ማህበሩ አባላትና የአካባቢው ማህበረሰብ በዕድር በደቦ እንዲሁም በመንፈሳዊ ማህበራት እንቅስቃሴዎች የኅብረትን ጥቅም ይተገብራሉ። ታዲያ ወደ ሎጁ የሚመጡ እንግዶች ልዩ አቀባበል ይጠብቃቸዋል። ሁሉም ከየቤቱ ባህላዊ ምግቡንና መጠጥ በማሰናዳት በምሽት ከሚንቀለቀለው እሳት ዙሪያ ከእንግዶች ጋር ያወጋል። የጋራ እሴቶቹን በኪነጥበብ ለዛ እያዋዛ ማህበራዊ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ መልዕክቱን በማስተላለፍ የማይዘነጋ ጊዜ ያኖራል።

የገነት ተፈጥሮ ሃብትና ቱሪዝም ኅብረት ስራ ማህበር በሙሉ ኢኮሎጂ የባህልና የሳይንስ ደሴት በመገንባት የሀገር በቀል እውቀትን በማደርጀት፤ተፈጥሮን በመንከባከብና ግብርናን በማዘመን ለትውልድ በማሸጋገር በድልድይነት ያገለግላል። የመዋዕለ ሕጻናት የትምህርት አገልግሎት የሚሰጡ ባህላዊ ይዘት ያላቸው ክፍሎች የተዘጋጁ ሲሆን የሀገር በቀል ዕውቀት በተረት ተረት አፈ ትምህርት ይሰጣል። እንዲሁም ወይዘሮ ባላሪና ሌሎችም የውጭ ሀገር ዜጎች በሚኖራቸው ቆይታ ቋንቋን በማስተማር ልዩ ጊዜን ያሳልፋሉ። ለዚሁ ትልም ስኬት የሙሉ ሎጅ አስተባባሪና የማህበሩ ሊቀመንበር የሆኑት አቶ መታደል አሳዬ ሕጻናት፣ሴቶችና ወጣቶች ሀገር ወዳድ እንዲሆኑ አሰራር ዘርግተን እየሰራን ነው ይላሉ።

ኅብረት ስራ ማህበሩ ራሱ ከሚያስተዳድረው ሙሉ ኢኮሎጂ ጋር ባለው የተቆራኘ እንቅስቃሴ ከተፈጥሮ ጥበቃና ከዘመናዊ ግብርና ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ውጤታማ ተግባራት ልምድ ማስተላለፊያ ማዕከል በመሆን አባላት የባለቤትነት ስሜት እንዲያድርባቸው እየሰራ ሲሆን፤ ለኅብረተሰቡም ማህበራዊ አገልግሎት በማበርከት ለኅብረት ስራ መርህ ታማኝ ሆኗል። የአካባቢው እናቶች እህል ተሸክመው ወፍጮ ቤት ፍለጋ በርቀት መጓዝን በማህበሩና በኅብረተሰቡ ጥረትና መደጋገፍ ታሪክ አድርገውታል። አገልግሎት በሚሰጡት የማህበሩ ሁለት የእህል ወፍጮዎች በጥቂት ክፍያና በቅርበት መገልገላቸውን ብዙሃን በደስታ ይናገራሉ።

ከግብርናና ከማኑፋክቸሪንግ ቀጥሎ መንግስት ትኩረት ካደረገባቸው መስኮች በዋናነት ጪስ አልባው ኢንዱስትሪ(ቱሪዝም) አንዱ የመሆኑን ያህል የገነት የተፈጥሮ ሃብትና ቱሪዝም ኅብረት ስራ ማህበር ትኩረትና ድጋፍ ቢሰጠው በዘርፉ ለሀገራዊ ጥቅም ጉልህ ሚና እንደሚኖረው ማየት ይቻላል። የመሰረተ ልማት ያለመሟላት ለአብነት ያህል የተስተካከለ መንገድ ያለመኖር ለጎብኚዎች መሰናክል በመሆኑና የኤሌክትሪክ ኃይል መሰረተ ልማት ባለመኖሩ በአካባቢው ያለውን እምቅ የቱሪዝም ሃብት መጠቀም ያልተቻለ ሲሆን የሚመለከታቸው አካላት መፍትሄ ቢሰጡበት መልካም ነው እንላለን።

አድራሻ | የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Federal cooperative Agency | Website: www.fca.gov.et